## 8. እግዚአብሔር; ቃሉና ባሕሪው- ልዑል ንጉስ – ክፍል 2

(የእግዚአብሔር ልኡላዊነትና የመንግስቱ መገለጥ)

---

በብሉይ ምንም እንኳ የእግዚአብሔር መንግሥት ባይብራራም ነገር ግን  የእግዚአብሔር አገዛዝ በፍጥረት; በሰማይና በምድር ባሉ ተቀሳቃሽ ፍጡራን; በዚህ ዓለም ላይ ባሉ መንግሥታትና ነገስታት ላይ እንደዚሁም ደግሞ በተለየ መልኩ በራሱ ፍጹም ነጻ የጸጋ አነሳሽነት ጠርቶና ዋጅቶ ገንዘቡ ባደረገው ሕዝቡ ላይ መንገሱ በይፋ ግልጽ ሆኖ የሚታይ ክስተት ነበር። ይህም የአንዱ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ መንግሥት ነው!

---

የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት (ጌትነንትና ገዢነት) በሁለት መልኩ ተገልጧል። ሉዓላዊ ጌትነት እግዚአብሔር ራሱን ለፍጥረቱ የሚገልጥበት መንገድ ነው። እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ በመፍጠር; በመመገብ; በመቤዠት ሆነ በመፍረድ እንደሚሰራ ተመልክተናል። እነዚህንም *ሥራዎች* ሲሰራ ለፍጥረቱ ***ጌትነቱን*** ለመግለጽ ነው።


- *ማሳሰቢያ:* ጌትነት የእግዚአብሔር የውስጥ ሕይወት ወደውጪ መንጸባረቁን ያመለክታል እንጂ በክበበ-ሥላሴ የውስጥ እርስበርስ ሕይወት የጌታና የሎሌ ግንኙነት የለውም። ይህ ግንኙነት *"ሁሉን የፈጠረው የሥሉሱ እግዚአብሔር"* እና *"የፍጥረቱ ግንኙነት ነው።"*
- ይህም ጌትነት/ልዕልና በሁለት መልኩ ይገለጻል።

    1. ***የሁሉ ጌታ:*** *ወሰን-መጠቅ/ሉዓላዊ ጌትነት* (Universal/Providential Kingdom) ሲሆን፡ ይህ መንግስት ሰማይንና ምድርን ያካለለ ነው; አገዛዙም ፍጥረቱን ሁሉ የሚሞላ ልዕልና ነው። በመንፈሱም በፍጥረቱ ወዲህና ወዲያ እየተንቀሳቀሰ ያስተዳድራል!

    2. ***የሕዝቡ ጌታ:*** *ታዳጊ/ ኪዳናዊ ጌትነት* (Particular/Redemptive Kingdom) ሲሆን ግዛቱ ገንዘቡ የሆነ ሕዝቡ ሲሆን; በሕላዌነቱ በመካከላቸው *በመረጠው ሥፍራ አብሯአቸው ይኖራል!*  በኤደን ለመጀመሪያውቹ ሰዎች ለአዳምና ለሔዋን; በመገናኛው ድንኳን ለእሥራኤል በምድረበዳ ; በጽዮን በቤተ-መቅደሱ ሥፍራ; በኢየሱስ ሰውነት ከመስቀል በፊት; ከተነሳ በኋላ ደግሞ በምድር በቤተክርስቲያን; በሰማይ "በአዲሲቱ ኢየስሩሳሌም/ ጽዮን ተራራ" በመጨረሻ ከሰማይ ወደምድር በምትወርደው አዲሲቱ ሰማይና አዲስቱ ምድር እግዚአብሔር እጅ ባልሰራው መቅደስ ከሕዝቡ ጋር ለዘላለም ይኖራል!

- ሁለቱም የሚገልጹት የአንዱ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሁለት ገጽታዎች ናቸው። እግዚአብሔር ለፈጠርው ፍጥረት ጌትነቱን ሲገልጽ ልዕልናውን በነዚህ በሁለት መልኮች ይገልጣል ማለታችን ነው።

እ/ር በትድግና ጌትነቱን ለሕዝቡ ሲገልጥ አላማው ጌትነቱን ለምድርና ለሰማይ ለመግለጥ ነው። ስለዚህ አጥብበን ያየነው የእግዚአብሔር አገዛዝ አላማው ጌትነቱን ለምድር ሁሉ ለመግለጥ ነው።



Note.....

a

## በመጀመሪያ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥነ-ል ታድያ ምን ማለታችን ነው?

- ***ሥልጣን*** ማለት የመግዛት መብት ማለት ነው (ምሳ፡ Luke 19፡ 11-12)
- **ሰማይና ምድር፡** ይህ አገላለጽ በተለያዩ አገባቦች የተለያዩ ትርጉሞች አሉት፡ ለምሳሌ
  1. ሰማይ በመጽሀፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍጹም ሥልጣን መመንጫ ሆኖ ወክሎ ሲገባ; ምድር ደግሞ ሥልጣኑ የሚገለጥበትን ክልል ይወክላል።

     **ኢሳ 66፡ 1-2፡***እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ሰማይ ዙፋኔ ነው፥ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት; የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድር ነው? 2 እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአብሔር;*
  2. ሰማይና ምድር፡ ጠቅላላ እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ይገልጻል

     **ዘፍ** 1:1 "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ"
  3. በአዲስ ኪዳን ሰማይ ኢየሱስ የማዳን ሥራውን ፈጽሞ ወደአባቱ የሁሉ ጌታ ይሆን ዘንድ ሲያርግ በግርማው ቀኝ የተቀመጠበት ሥፍራ ነው። እስኪመለስ ድረስ በዚያ ሆኖ ይቆያል። በዚህ ሥፍራ አሁን ቤተክርስቲያንን ራስ ሆኖ የሚያስተዳድርበት የሽግግር መንግሥት ነው። (ሐዋ 3፡ 21;)

     Ephesians 1:20–23 ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል; 22 ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው። 23 እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት።
- ***መንግሥት፡*** ስለ እግዚአብሔር መንግስት መጽሀፍ ቅዱስ ሲናገር

1. **በአገዛዝና በግዛት ክልል መካከል ያለው ልዩነት፡**
   1. **አገዛዝ፡** በመጀመሪያ ደረጃ የሚናገረው ስለ "አስተዳደር" ወይም አገዛዝ Sovereign rule ሲሆን።

      **Ps** 145:11–13

      "ሥለ ***መንግሥትህ*** ክብር ይናገራሉ፥
      "ሥለ ***ኃይልህም*** ይነጋገራሉ፥
      በዚህም ብርቱ ሥራህን;
      የመንግሥትህን ግርማ ክብር ያስታውቃሉ
      ***መንግሥትህ*** የዘላለም መንግሥት ናት፥
      ***ግዛትህም*** ለልጅ ልጅ ነው።"

      **ዳንኤል** 4:3–4

      3 *ተአምራቱ እንዴት ታላቅ ነው!*
      *ድንቁም እንዴት ጽኑ ነው!*
      ***መንግሥቱም*** *የዘላለም መንግሥት ነው፥*
      ***ግዛቱም*** *ለልጅ ልጅ ነው።*

      **Luke 17:20**

      *"ፈሪሳውያንም። የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች ብለው ቢጠይቁት፥ መለሰ። የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም; 21 ደግሞም። እንኋት በዚህ ወይም። እንኋት በዚያ አይሉአትም። እነሆ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና አላቸው።"*

      **ቆላ** 1:13–14

      እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።

Note.....

a

2. **የግዛት/ የመናገሻ ክልል፡** በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አገዛዙ የሚገለጥበትን ክልል (Realm)ለማመልከት ነው። እግዚአብሔር ምንም እንኳ ምጡቅ እንደመሆኑ በቦታና በሥፍራ ሊወሰን የማይችል መንፈስ የሆነ አምላክ ቢሆንም ነገር ግን ለሕዝቡ ራሱን የሚገልጥበትና ሕዝቡን ይመራ ዘንድ አብሯቸው የሚኖርበት መናገሻ ሥፍራን ይከልላል። ከብሉይ ወደአዲስ ያለው እንቅስቃሴ ከእስራኤል ክልል ጀምሮ እየሰፋ ዓለምን ሁሉ የሚሞላ እንቅስቃሴ ነው።

**ማቴ 8:11–13** “እላችኋለሁም፥ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ; 12 የመንግሥት ልጆች ግን በውጭ ወደ አለው ጨለማ ይጣላሉ; በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። 13 ኢየሱስም ለመቶ አለቃ። ሂድና እንዳመንህ ይሁንልህ አለው። ብላቴናውም በዚያች ሰዓት ተፈወሰ።”

**ማቴ** 13:41–42 “የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፥ *ከመንግሥቱም* እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፥ 42 ወደ እቶነ እሳትም ተጣሉ

**ማቴ** 26:26–29 “ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና። እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። 27 ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ። ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ; 28 ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው። 29 ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም።አቸዋል; በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።”

**ራዕ 5:9–10** መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ።

**ራዕ 11:15–17** “ሰባተኛው መልአክ ነፋ; በሰማይም። የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል 16 የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ሆኑ። በእግዚአብሔርም ፊት በዙፋኖቻቸው የተቀመጡ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በግምባራቸው ተደፍተው 17 ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ። ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን;”

**ራዕ 21:1–8** አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም። 2 ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። 3 ታላቅም ድምፅ ከሰማይ። እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል; 4 እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ። 5 በዙፋንም የተቀመጠው። እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም። እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞች ናቸውና ጻፍ አለኝ። 6 አለኝም። ተፈጽሞአል። አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ። 7 ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል። 8 ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኛዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኛዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው; ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።

Note.....

a

**2. በወሰን-መጠቅ አገዛዝና በኪዳናዊ አገዛዝ (በሁሉ-ጌትነቱና በህዝቡ ገጌትነቱ) መካከል ያለው ልዩነት፡**

1) **ወሰን-መጠቅ ጌትነት፡** ይህን ጌትነት እግዚአብሔር ሁሉን በመፍጠር የተጎናጸፈው ጌትነቱ ነው። ከዚህ የተነሳ ሁሉም በመንግሥቱ አስተዳደር ሥር ነው። ሁሉ የተፈጠረ ዘንድ እስከሆነ ድረስ እግዚአብሔር በሁሉ ላይ ጌታ ነው። ይህ ንጉስ እጅግ ምጡቅ ንጉስ መሆኑን ያሳየው *"እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ… ብርሃንም ሆነ!"* በውሳኔ ቃል *መንግሥቱን ዘርግቶ የነገሠ ልዩ ገዢ ነው! ስለዚህ በዚህ መልኩ ስናየው ማንም ወደ መንግስቱ ይገባል አይባልም ምክኒያቱም ሁሉም በመንግሥቱ ውስጥ ነው። የዚህ አገዛዝ መገለጫው የመግቦት ሥራው ነው።* ይህም እግዚአብሔር ከነገስታት; ከሑነቶች ጀርባ ሆኖ የሚገልጸው አስተዳደር ነው! በዚህ አገዛዙ በምድር ተንሳርፍቶ ያለውን አመጽ ይቆጣጠራል; ክፍትን ከዚህ አትለፍ ይለዋል። ሕዝብን ሊቀጣና ፍርዱን ሊገልጽ ዘላለማዊ ሐሳቡን ከታሪክ ጋር ሊያቀናብር ክፉትንና አመጽን በአንድ ወቅት እንዲሰፍኑ ይፈቅዳል (ኢሳ 45፡ 1-7)።

> **Psalm 103:19–22** እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፥ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች። 20
> ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥
> እግዚአብሔርን ባርኩ። 21 ሠራዊቱ ሁሉ፥ ፈቃዱን የምታደርጉ አገልጋዮቹ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ።
> 22 ፍጥረቶቹ ሁሉ በግዛቱ ስፍራ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ። ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ።
>
> **Psalm 145:13** መንግሥትህ የዘላለም መንግሥት ናት፥ ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው።
>
> **Psalm 47:2** እግዚአብሔር ልዑል ግሩምም ነውና፥ በምድር ሁሉ ላይም ታላቅ ንጉሥ ነውና።
>
> **Daniel 2:37** አንተ፥ ንጉሥ ሆይ፥ የሰማይ አምላክ መንግሥትንና ኃይልን፥ ብርታትንና ክብርን የሰጠህ የነገሥታት ንጉሥ አንተ ነህ።
>
> **Daniel 5:21** ልዑል አምላክም በሰዎች መንግሥት ላይ እንዲሠለጥን፥ የሚወድደውንም እንዲሾምበት እስኪያውቅ ድረስ ከሰው ልጆች ተይለቶ ተሰደደ፥ ልቡም እንደ አውሬ ልብ ሆነ፥ መኖሪያውም ከምድረ በዳ አህዮች ጋር ነበረ; እንደ በሬ ሣር በላ፥ አካሉም በሰማይ ጠል ረሰረሰ።

2) **ኪዳናዊ አገዛዝ፡** ምንም እንኳ እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ንጉሥ ቢሆንም ነገር ግን ንግሥናው ተቀናቃኝና አልገዛም ባይ ጠላቶች አሉት። ነገር ግን ከነዚህ አመጸኞች መካከል በጸጋው ወደርሱ እየጠራ ገንዘቡ ባደረጋቸው ሕዝቡ ላይ በማዳን ይነግሳል። በሁሉቱ ጌትነቱ መካከል ልዩነቱ ይህ ንግሥና "መዋጀትና መዳን" ያለበት የንግሥና ክልል ነው። ለዚህ ነው ኒቆዲሞስን ኢየሱስ ዳግም ካልተወለድህ በስተቀር የእግዚአብሔርን መንግስት አታያትም ያለው!

> Exodus 6:5–7 (AMHB)
>
> 5 ደግሞ እኔ ግብፃውያን የገዙአቸውን የእስራኤልን ልጆች ልቅሶ ሰማሁ; **ቃል ኪዳኔንም አሰብሁ።** 6
> ስለዚህም ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው። እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ከግብፃውያንም ባርነት
> አወጣችኋለሁ፥ ከተገዥነታቸውም አድናችኋለሁ; በተዘረጋ ክንድ በታላቅ ፍርድም እታደጋችኋለሁ፥
> **7 ለእኔም ሕዝብ እንድትሆኑ እቀበላችኋለሁ፥ አምላክም እሆናችኋለሁ;** እኔም ከግብፃውያን ባርነት
> ያወጣኋችሁ **እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደሆንሁ ታውቃላችሁ።**
>
> Daniel 2:44–47 (AMHB)
>
> 44 በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል; ለሌላ
> ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል; እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች
> ታጠፋቸውማለች፥ ለዘላለምም ትቆማለች። 45 ድንጋዩም እጅ ሳይነካው ከተራራ ተፈንቅሎ
> ብረቱንና ናሱን ሸክላውንና ብሩን ወርቁንም ሲፈጨው እንዳየህ፥ እንዲሁ ከዚህ በኋላ የሚሆነውን
> ታላቁ አምላክ ለንጉሡ አስታውቆታል; ሕልሙም እውነተኛ ፍቺውም የታመነ ነው።…47 ንጉሡም
> ዳንኤልን። ይህን ምሥጢር ትገልጥ ዘንድ ተችሎሃልና በእውነት አምላካችሁ የአማልክት አምላክ፥
> የነገሥታትም ጌታ፥ ምሥጢርም ገላጭ ነው ብሎ ተናገረው።
>
> **የእግዚአብሔር መንግስት ትነሳለች። እንደምጡቅ-ንግሥናው መንግስቱ አትመሰረትም; ሰማይና ምድርን የፈጠረ ዕለት ጀምሮ የተዘረጋ መንግሥት ናት; ነገር ግን በተለየ መልኩ ደግሞ ትዘራለች ትነሳለች! ይህ የኪዳናዊ አገዛዙ ነው!**

Note.....

a

እኔም። ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፥ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል
በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ! አልሁ።

**Isaiah 43:15–19** ቅዱሳችሁ፥ **የእስራኤል ፈጣሪ፥** ንጉሣችሁ፥ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። 16
እግዚአብሔር በባሕር ውስጥ መንገድን በኃይለኛም ውኃ ውስጥ መተላለፊያን ያደርጋል; 17
እግዚአብሔር ሰረገላውንና ፈረሱን ሠራዊቱንና አርበኛውን ያወጣል; እነርሱ ግን በአንድነት
ተኝተዋል፥ አይነሡም; ቀርተዋል፥ እንደ ጥዋፍ ኩስታሪም ጠፍተዋል; እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።
18 የፊተኛውን ነገር አታስተውሉ፥ የጥንቱንም ነገር አታስቡ። 19 እነሆ፥ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ;
እርሱም አሁን ይበቅላል፥ እናንተም አታውቁትምን? በምድረ በዳም መንገድን በበረሀም ወንዞችን
አደርጋለሁ።

**Numbers 23:21–23** "በያዕቆብ ላይ ክፋትን አልተመለከተም፥ በእስራኤልም ጠማምነትን አላየም;
አምላኩ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነው፥ የንጉሥም እልልታ በመካከላቸው አለ። 22 እግዚአብሔር
ከግብፅ አውጥቶአቸዋል;ጕልበቱ እንድ ቀንድ እንዳለው ነው። 23 በያዕቆብ ላይ አስማት የለም፥
በእስራኤልም ላይ ምዋርት የለም; በጊዜው ስለ ያዕቆብና ስለ እስራኤል። እግዚአብሔር ምን አደረገ!
ይባላል።"

ማቴዎስ 13:37–42 (AMHB)

37 እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው። መልካምን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው; እርሻውም ዓለም ነው;
38 መልካሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው; 39 እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፥ የዘራውም
ጠላት ዲያብሎስ ነው; መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፥ አጫጆችም መላእክት ናቸው። 40 እንግዲህ
እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል፥ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል። 41 የሰው ልጅ
መላእክቱን ይልካል፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፥ 42 ወደ
እቶነ እሳትም ይጥሉአቸዋል; በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

ማቴዎስ 28:18–20 (AMHB)

18 ኢየሱስም ቀርቦና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። 19-20
እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥
ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው; እነሆም እኔ እስከ
ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

### 3. በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጌትነትና በዘመናችን በሪፐብሊክ አገዛዝ መካከል ያለውን ልዩነት

እግዚአብሔር የዲሞክራሲ አመራር የለውም። በብዙሀኑ ሐሳብ አያምንም። አሁን ባለንበት ዓለም ሕዝብ የመረጣቸውና የሕዝቡን ፈቃድ ለማገልገል የተሾሙ መሪዎች አሉ። በብዙሁኑ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ የመንግሥት መተዳደሪ ሕግ "ሕገ-መንግሥት" ይጻፍና በዚያ መንግሥት ሕዝቡን ያስተዳድራል። ይህ አይነት የመንግሥት አሰራር ፍልስፍና የመንጨው ከክርስቶስ ልደት ከ500 ዓመታት በፊት ሲሆን የቃሉ ምንጭ δημοκρατία (dēmokratía) "የሕዝብ አመራር" ማለት ሲሆን ከሁለት ጥምር ቃላቶች የወጣ ነው። ይህም δῆμος (dêmos) "ሕዝብ" ማለት ሲሆን κράτος (kratos) "ሐይል/ ሥልጣን/ አመራር ማለት ነው። የጥንታዊው አለም ነገስታት ይህ ለንግስናቸው እንደመሳለቂያ ነው።ምክኒያቱም ነገስታት ይገዛሉ እንጂ አይመከሩም። ነገስታት ሕግ ያወጣሉ እንጂ ሕግ በነሱ ላይ አይሰራም። ንጉሱ ራሱ ሕግ በመሆኑ ንጉሱ የተናገረው ነገር ሕግ ሆኖ የታወጀል። መንግስታቸውም መለዮ ዘውዳዊ "ሞናርኪዝም" ነው; ሕጋቸውም ፍትሐ ነገሥት ሆኖ ይጻፋል።

አሁን ባለንበት ዓለም ያሉ ነገስታቶች ግን የመጽሀፍ ቅዱስን ንግሥና ባለማንጸባረቁ ይህንን ልዩነት ማምጣት ተገቢ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የአሁኑ አይነት ንግሥና የመነጨው በተለይ በአሜሪካና በፈረንሳይ ከተንሳው የአብዮት እንቅስቃሴ ነው። ነገሥታት እጅጉን መረን ከመልቀቅ አልፈው ሕዝብን በመጨቆን በፍጹም ጭከና ሲመሩ የተነሳ አብዮት ነው።፡ይህ የነጻነት-ትግል አሁን በአሜሪካ ያለውን አይነት ዲሞክራሲ እንዲሰራፋ አድርጓል። በአለም የቀሩትም ጥቂት ነግሥታት መንግሥታቸው "ሕገ-መንግሥታዊ ንግስና "Constitutional monarchs" በመባል ይታወቃል። ምክኒያቱም ሥልጣናቸውን ለመለማመድ ሕዝብ ባጸደቀው ሕገ-መንግሥት ሥር ብቻ ስለሚተዳደሩ ነው። አሁን በእንግሊዝ አገር ያለችው ንግስት "ኤልሳቤት" ከምልክትነት በስተቀር ብዙ ስልጣን የላትም። ምክኒያቱም ሥልጣኗ በእንግሊዝ ሕገ መንግሥት ሥር ስለሆነ ነው።

Note.....

a

ይህ ዳራ/ context ከመጽሀፍ ቅዱሱ ንግሥና የተለየ ነው። እግዚአብሔር ሉዓላዊ ንጉስ ነው። ሥልጣኑ ፍጹም በመሆኑ ይግባኝ የሌለው የሥልጣን ጣራ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ንግሥና ምን ይመስላል? ለምሳሌ አድርገን ኢሳ 33፡22ን እንመልከት፡

**ኢሳያስ 33:22**

22 እግዚአብሔር ***ፈራጃችን*** ነው፥
እግዚአብሔር **ሕግን** ሰጪያችን ነው፥
እግዚአብሔር **ንጉሣችን** ነው;
እርሱ ያድነናል።

ይህ አሁንም የዕብራይስጥ ግጥም ነው። ፈራጃችን; ሕግን ሰጪያችንና ንጉሣችን ተመሳሳይ ናቸው። ኢሳያስ ይህን የተናገረው የእግዚአብሔር ምጡቅ-ልዕልናው በሰማያት እንደተዘረጋ ወደፊት ዙፋኑን በሙላት በጽዮን እንደሚያመጣ ሲናገር *“5እግዚአብሔር በአርያም ተቀምጦአልና ከፍ ከፍ አለ; ጽዮንን በፍርድና በጽድቅ ሞላት።”* እግዚአብሔር ፈጥኖ ስለሚገልጠው ማዳንና ስለሚያመጣውም ዓለም-ዓቀፍ ደህነት *“10 አሁን እነሣለሁ ይላል እግዚአብሔር; አሁን እከበራለሁ; አሁን ከፍ ከፍ እላለሁ”* ውጤቱም *“17ዓይኖችህ ንጉሥን በውበቱ ያዩታል; እነርሱም በሩቅ ያለች ምድርን ያዩአታል”* ራሱ እግዚአብሔር በሙላት ወርዶ ዓለምን ይገዛል! ይህም ፍጹም አገዛዝ በነዚህ ሦስት ቃላቶች ተገልጿል; *ፈራጅ; ሕግ ሰጪ; ንጉሥ።* The three branches of government

ቅድም እንደተመለከትነው በዘመናችን እነዚህ ሦስቱም በአንድ ሰው ጫንቃ ላይ አይገኙም። ቢገኙ እነዚህን አምባገነን መሪዎች / dictators/ እንላቸዋለን። ለዚህ ነቀፌታ በቂ ምክኒያት አለን። ሰዎች በጽድቅ መግዛት ስላማይችሉ ነው። ለምሳሌ በአሜሪካን ኮንስቲቲውሽን መሰረት የሥልጣን ክፍፍል ( balance of power) አለ። The executive branch, the judiciary branch and the legislative branch.

እግዚአብሔር አምላካችን ግን ንጉሳችን (መሪ; ገዢ; ጌታችን); ሕግ ሰጪ እና ዳኛችን ነው። በአጭር ቃል አምላካችን ፍጹም ንጉስ ነው!

የመዝሙር መጽሀፍ በአንድ ላይ ጠርዞ ያቀናበረው ሰው ስለዚህ ንግሥና ባህሪይ ተረድተው የእሥራኤል ዘማሪዎች የዘመሩትን መዝሙሮች ከPs 93 - Ps 100 በአንድላይ አስቀምጧቸዋል። ለምሳሌ ያህል፡

**Psalm 93:1–2 (AMHB) ንግሥናውን ያጎላል በተለይ ምጡቅ-ንግሥናውን (ፈጣሪነቱ)**

1 እግዚአብሔር ነገሠ፥ ክብርንም ለበሰ; እግዚአብሔር ኃይልን ለበሰ፥ ታጠቀም; ዓለምን እንዳትናወጥ አጸናት። 2 ዙፋንህ
ከጥንት ጀምሮ የተዘጋጀ ነው፥ አንተም ከዘላለም ነህ።

**Psalm 94:1–2 (AMHB) ዳኛነቱን ያጎላል**

1 እግዚአብሔር የበቀል አምላክ ነው። የበቀል አምላክ ተገለጠ። 2 የምድር ፈራጅ ሆይ፥ ከፍ ከፍ በል; ለትዕቢተኞች
ፍዳቸውን ክፈላቸው።

**Psalm 95:3–5 (AMHB) ንግሥናው ወሰን-መጠቅ መሆኑንና ሰዎች ለኪዳን ጌትነቱ በመገዛት ወደ እረፍቱ እንዲገቡ ያዛል**

3 እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ነውና፥ በአማልክትም ሁሉ ላይ ታላቅ ንጉሥ ነውና። 4 እግዚአብሔር ሕዝቡን
አይጥላቸውም; የምድር ዳርቻዎችም በእጁ ውስጥ ናቸው፥ የተራሮች ከፍታዎች የእርሱ ናቸው። 5 ባሕር የእርሱ ናት
እርሱም አደረጋት፥ የብስንም እጆቹ ሠሩአት። 6 ኑ፥ እንስገድ ለእርሱም እንገዛ; በእርሱ ባደረገን በእግዚአብሔር ፊት
እንበርከክ; 7 እርሱ አምላካችን ነውና፥ እኛ የማሰማርያው ሕዝብ የእጁም በጎች ነንና። 8 በምድረ በዳ እንደ ተፈታተኑት
እንዳስቈጡት ጊዜ፥ ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ ልባችሁን አታጽኑ። 9 የተፈታተኑኝ አባቶቻችሁ ፈተኑኝ ሥራዬንም አዩ። 10
ያችን ትውልድ አርባ ዓመት ተቈጥቻት ነበር። ሁልጊዜ ልባቸው ይስታል፥ እነርሱም መንገዴን አላወቁም አልሁ። 11 ወደ
ዕረፍቴም እንዳይገቡ በቍጣዬ ማልሁ።

Note.....

a

Psalm 96:9–13 (AMHB) ***ይህ መዝሙር የእግዚአብሔር ኪዳናዊ ጌትነት ከእስራኤል ዳርቻ ባሻገር እንደሚዘረጋ ያሳያል!***

9 በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ; ምድር ሁሉ በፊቱ ትነዋወጥ። 10 በአሕዛብ መካከል። እግዚአብሔር ነገሠ በሉ።
እንዳይናወጥም ዓለሙን እርሱ አጸናው፥ አሕዛብንም በቅንነት ይፈርዳል። 11 ሰማያት ደስ ይበላቸው፥ ምድርም ሐሤትን
ታድርግ; ባሕርና ሞላዋ ይናወጡ; 12 በረሃ በእርስዋም ያሉ ሁሉ ሐሤትን ያድርጉ; የዱር ዛፎች ሁሉ በዚያን ጊዜ
በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይላቸዋል; 13 ይመጣልና; በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣልና; እርሱም ዓለምን በጽድቅ አሕዛብንም
በቅንነት ይፈርዳል።

**Psalm 97:1–2 (AMHB) እግዚአብሔር ለእስራኤል እንደተገለጠላት ለምድር ሁሉ እንደሚገለጥ ያኅላል**

1 እግዚአብሔር ነገሠ; ምድር ሐሤትን ታድርግ፥ ብዙ ደሴቶችም ደስ ይበላቸው። 2 ደመና ጭጋግም በዙሪያው ናቸው;
ጽድቅና ፍርድ የዙፋኑ መሠረት ናቸው።...7 ለተቀረጸ ምስል የሚሰግዱ ሁሉ፥ በጣዖቶቻቸውም የሚመኩ ይፈሩ; መላእክቱ
ሁሉ፥ ስገዱለት። 8 አቤቱ፥ ስለ ፍርድህ ጽዮን ሰምታ ደስ አላት፥ የይሁዳም ሴት ልጆች ደስ አላቸው; 9 አንተ፥
እግዚአብሔር፥ በምድር ላይ ሁሉ ልዑል ነህና፥ በአማልክትም ሁሉ ላይ እጅግ ከፍ ከፍ ብለሃልና።

Psalm 98:5–9 (AMHB)

5 ለእግዚአብሔር በመሰንቆ፥ በመሰንቆና በዝማሬ ድምፅ ዘምሩ። 6 በዋሽንትና በመለከት ድምፅ በንጉሥ በእግዚአብሔር
ፊት እልል በሉ። 7 ባሕርና ሞላዋ፥ ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ይናወጡ። 8 ወንዞችም በአንድነት በእጅ ያጨብጭቡ;
ተራሮች ደስ ይበላቸው፥ በምድር ሊፈርድ ይመጣልና። 9 ለዓለምም በጽድቅ ለአሕዛብም በቅንነት ይፈርዳል።

Psalm 99:1–5 (AMHB)

1 እግዚአብሔር ነገሠ፥ አሕዛብ ይደንግጡ; በኪሩቤል ላይ ተቀመጠ፥ ምድር ትናወጥ። 2 እግዚአብሔር በጽዮን ታላቅ ነው;
እርሱም በአሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ አለ። 3 ግሩምና ቅዱስ ነውና ሁሉ ታላቅ ስምህን ያመስግኑ። 4 የንጉሥ ክብር ፍርድን
ይወድዳል; አንተ ቅንነትን አጸናህ፥ ለያዕቆብ ፍርድንና ጽድቅን አንተ አደረግህ። 5 አምላካችንን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ
አድርጉት፥ ቅዱስ ነውና ወደ እግሩ መረገጫ ስገዱ።

Psalm 100:1–5 (AMHB)

1 ምድር ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር እልል በሉ፥ 2 በደስታም ለእግዚአብሔር ተገዙ፥ በሐሤትም ወደ ፊቱ ግቡ። 3
እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ እወቁ; እርሱ ሠራን እኛም አይደለንም; እኛስ ሕዝቡ የማሰማርያውም በጎች ነን። 4
ወደ ደጆቹ በመገዛት፥ ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ; አመስግኑት፥ ስሙንም ባርኩ; 5 እግዚአብሔር ቸር፥ ምሕረቱም
ለዘላለም፥ እውነቱም ለልጅ ልጅ ነውና።

ይህ ማለት የሰዎችን ምክር ምክሩ አይደርግም ይልቁንስ ዘላለማዊ ስሉስ-ምክሩን ሕግ አድርጎ ደንግጓል። ምክሩን ያጸናል (ኢሳ 7:7; 25:1; 28:29; 30:1; )።፡ጻድቃንም በምክሩ ይኖራሉ "Psalm 1:1–3 ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ ...ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል።"

Psalm 33:8–12 ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው፥ እርሱ ተናግሮአልና፥ ሆኑም; እርሱ አዘዘ፥ ጸኑም።
እግዚአብሔር የአሕዛብን ምክር ያጠፋል፥ የአሕዛብንም አሳብ ይመልሳል። 11 የእግዚአብሔር ምክር ግን
ለዘላለም ይኖራል። የልቡም አሳብ ለልጅ ልጅ ነው። 12 እግዚአብሔር አምላኩ የሚሆንለት ሕዝብ
ምስጉን ነው፥ እርሱ ለርስቱ የመረጠው ሕዝብ።"

### 4. በኪዳኑ መንግሥት መገለጥና በፍጻሜው መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ

ምንም እንኳ የእግዚአብሔር መንግሥት በልጁ በክርስቶስ መምጣት ብትገለጥም ነገር ግን ፍጻሜው ገና አልመጣም! ይህም የእግዚአብሔርን ሐሳብ በሁለት ዘመናት እንዲከፈል አድርጎታል! አዲስ ኪዳን ስለ እግዚአብሔር ኪዳናዊ መንግሥት ሲናገር በሁለት መልኩ ያስቀምጠዋል።

ማቴዎስ 5:3 (AMHB) 3 በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።

ማቴዎስ 6:9–10 (AMHB)

9 እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ። በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥ 10 ስምህ ይቀደስ;
መንግሥትህ ትምጣ; ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን;

Note.....

a

### መንግሥቱ መጥታለች ደግሞም ትመጣለች

የሁለቱ ልዩነት የተመሰረተው በንጉሱ/ በክርስቶስ ነው። ይህም በምድር ክርስቶስ ሲመላለስ መንግሥቱ ቀርባለች; ነገርግን ክርስቶስ ወደ አባቱ ከተመለሰ በኋላ ግን ዳግም እስኪመጣ ድረስ መንግሥቱን እንጠባበቃለን። ሁለቱም በአሁኑ ዘመን እውነት ነው። ሁኖም ግን ክርስቶስ ከምድር ሳይሆን ከአባቱ ቀኝ ሆኖ ንግሥናውን ይገልጣል። ይህ በአዲስ ኪዳን ጳውሎስ በኤፌሶን "ሰማያዊው ሥፍራ" የሚለው ነው። ነገር ግን በምድር ላይ ኪዳናዊ መንግሥቱ "እንደ እኔ ያለ ሌላ አጽናኝ" ተብሎ ተስፋ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ መምጣት አሁን ክርስቶስ መንግስቱን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ይገልጣል።

ይህንን ልዩነት ነብያት ያላዩት ሚስጥር ነበር! ዮሐንስን ጨምሮ። ምክኒያቱም ኢየሱስ ሲያደርግ የሰማው የማዳንን ሥራ ብቻ ሲሰራ እንጂ ክርስቶስ ሲገለጥ ይሰራዋል ተብሎ የሚጠበቀውን የፍርድን ሥራ አልገለጠም። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሆነ ለምን የብረትን በትሩ ዮሐንስን እስር በከተተት በሮማውያን ገገሮች ላይ አይገለጥም? ይህ ጥያቄ ነበር መልዕክተኞችን እንዲልክ ግድ ያስባለው፡

> ማቴዎስ 11:2–6 ዮሐንስም በወህኒ ሳለ የክርስቶስን ሥራ ሰምቶ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከና። 3 **የሚመጣው አንተ ነህን? ወይስ ሌላ እንጠብቅ? አለው።** 4 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት; 5 ዕውሮች ያያሉ አንካሶችም ይሄዳሉ፥ ለምጻሞችም ይነጻሉ ደንቆሮችም ይሰማሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ 6 ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል; በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው።

### የሚመጣው የመሲሑ መንግሥት

ስለዚህ እግዚአብሔር ነግሥናው ፍጹም ንግሥና ሲሆን አንድ ቀን ደግሞ ኪዳናዊ ጌትነቱ/ንግሥናው በምድር ሁሉ ላይ ይገለጣል!

ብሉይ ኪዳን ስለዚህ መንግሥት ሲመሰክር፡

1) **መሲሐዊ መንግሥት**
   a) **የዳዊት ልጅ/ ንጉስ** (ቁጥቋጥ/የእሴይ ግንድ) 69; 2 Sam. 7:11–13, 16; Ps. 89:4; 132:11; Isa 4:2; 9:6, 7; 11፡ 1-2; 16:5; Acts 2:30; 13፡ 23 [Rev. 3:7]
   b) Jeremiah 23:5-8; Ge 18:19; Ezekiel 17:22-24; Jer 30:9; Isa. 32:1; Ezek. 37:24; Hos. 3:5; Zech. 9:9; Matt. 2:2; Luke 1:32; 19:38; John 1:49; Je 33:15; Zech 3: 8; 6: 12
   c) **እረኛ** Eze 34: 23; 37:22, 24; Jer. 23:4, 5; Mic 5:4; 7:14; john 10:11, 16; zech 3:8)
   d) **የሰው-ልጅ** (dan 7፡9-10; 13-14; ps 8:6; Matt. 26:64; Heb 2፡6-10 Rev. 1:7; 14:14)
   e) **ጌታ** ps 110:1-2; Isa. 9:6, 7; Rev. 11:15)
   f) **የጌታ ባርያ** (isa 42: 1-4; 49: 1-6; 50: 4-9; 52:13-53:12)
   g) **የተቀባ/ ክርስቶስ፡** በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ ንጉስ ይሆናል! መንፈስ ያርፍበታል (Lk 4:18; Ac 10:38; Heb 1:9
2) **መሲሐዊ ዘመን (ኢሳ 11)**
   a) አዲስ ዘጸዓት ይገለጣል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብጽ እንዳወጣ ለሁለተኛና ለመጨረሻ ጊዜ ህዝቡን ይሰበስባል (Isa 11፡ 11-16)
   b) ንግሥናውና አለቅነቱ በምድር ሁሉ ላይ ይሆናል (Dan. 2:44; 7:14, 18, 27; Zechariah 9:9-10; Psalm 72:8-11 ;Heb. 1:8; Rev. 11:15)

Note.....

a

c) የእግዚአብሔር መገኘት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መመለስና የቤተ/ መቅደሱ እንደገና በክብር ይሞላል! (Isa 2፡1-4)

d) እግዚአብሔር አዲስ ኪዳን እንደገና ከሕዝቡ ጋር ይገባል; *አዲስ ዘጸዓት; አዲስ ኪዳን; አዲስ መንፈስ* (Jer 31:21-34; Ezek. 37:26)

e) የእግዚአብሔር መንግሥት በሃይል ትገለጣለች

f) ዓለም አቀፍ ትድግ ይገለጣል

g) ፍጥረት ሁሉ ከሐጥያት; ከሞትና ከአመጽ እጅ ነጻ ሆኖ አዲስ ይሆናል (Isa 65-66; Rev 21-22)

## ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (የዳዊት/የእግዚአብሔር ልጅ/ መሢህ ነው)

*እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። [16] ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ። አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። ...ማቴ 16*

ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ። ሲጸልይም ሰማይ ተከፈተ፥ [22] መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ; ***የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ በአንተ ደስ ይለኛል*** የሚል ድምፅም ከሰማይ መጣ።

ኢየሱስ በሰዎች ዓይን የዮሴፍ የአናጺው ልጅ ቢባልም በአባቱ ዓይን ግን የሚወደው ልጁ ነው።።የአብ ምሥክርነት ሦስት የመጽሀፍ ቅዱስ ተስፋ ፍጻሜ ነው። ሆኖም እጅግ አስደናቂ የሚያደርገው እነዚህ ታላላቅ ተስፋዎች አሁን በአንድ ሰው ላይ መጋጠማቸው ነው። አባቱ ለልጁ ለኢየሱስ ያለበሰው ማንነት በነዚህ ሦስት ማንነቶች ላይ ያተኮረ ነው።

1. ***"በአንተ ደስ የሚለኝ"*** - **የእግዚአብሔር አገልጋይ ተስፋ በኢሳያስ 40-55** ኢሳ 42፡ 1-9/ ኢሳ 49፡ 1-6/ 50፡ 4-10/ 52፡ 13-53:12። የዚህ አገልጋይ ተል ዕኮውን የሚወጣው በጦር/ በሃይል ሳይሆን በመሰቃየት በመጨነቅ; በመጣልና በመሞት ነው። ይህ አገልጋይ የእግዚአብሔር ሃሳብ በእጁ የምትከናወን የእስራኤልን ተስፋ ፍጻሜ የሚያደርስ

2. ***"የምወድህ"***... ዘፍ 22፡ 2 *"[2] የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ; እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ።"* ለመስዋዕት የሚቀርበው አባቱ የሚወደው ልጅ።።አብርሃም የሚወደውን አንድያ ልጁን ሊሰዋ ይስሐቅም አባቱ ሊታዘዝ መስዋዕት እንደሆን ኢየሱስም አባቱ የሚወደው ለብዙዎች መስዋዕት ይሆን ዘንድ የሚቀርብ የመስዋዕቱ በግ ነው። ለይስሐቅ ምትክ አውራ በግ ቢሰጠውም ኢየሱስ ግን በመስቀል ላይ ተተወ። ...የመስዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል...ያህዌ ይርኢ ሮሜ 8፡ 32

3. ***"አንተ ልጄ ነህ"*** Ps 2፡ 7 2Sam 7፡ 14; 2 sam 23፡ 1-7; Ps 89; 1-52; Ps 132፡ 10-14 Luke 1፡ 32; Luke 3፡ 22/ ሐዋ 2፡ 30-31; ሐዋ 4፡ 25-28; ሐዋ 13፡ 32-33/ ዕብ 1፡ 5; ዕብ 5፡ 5

**Ps 2:7**

ትእዛዙን እናገራለሁ; እግዚአብሔር አለኝ። አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ።

**2 ሳሙ 7:14**

እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል; ክፉ ነገርም ቢያደርግ፥ ሰው በሚቀጣበት በትርና በሰው ልጆች መቀጫ እገሥጸዋለሁ;

**Ps 132:10–14**

11 እግዚአብሔር ለዳዊት በእውነት ማለ አይጸጸትምም፥ እንዲህ ብሎ። ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ።

**Luke 1:32**

እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል;

**Luke 3:22**

*መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ; የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅም ከሰማይ መጣ።*

**ሐዋ 4:25–28**

25 በመንፈስ ቅዱስም በብላቴናህ በአባታችን በዳዊት አፍ። አሕዛብ ለምን አጕረመረሙ? ሕዝቡስ ከንቱን ነገር ለምን አሰቡ? 26 የምድር ነገሥታት ተነሡ አለቆችም በጌታና በተቀባው ላይ አብረው ተከማቹ ብለህ የተናገርህ አምላክ ነህ። 27–28 በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ በኢየሱስ ላይ ሄሮድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር፥ እጅህና አሳብህ እንዲሆን አስቀድመው የወሰኑትን ሁሉ ሊፈጽሙ፥ በዚች ከተማ በእውነት ተሰበሰቡ።

Note.....

a

**ሐዋ 13:32–33**

32 እኛም ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ የምስራቹን
ለእናንተ እንሰብካለን; 33 ይህን ተስፋ እግዚአብሔር
በሁለተኛው መዝሙር ደግሞ። **አንተ ልጄ ነህ እኔ
ዛሬ ወለድሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ኢየሱስን
አስነሥቶ ለእኛ ለልጆቻቸው ፈጽሞአልናል።**

**ዕብ 1:5**

ከመላእክትስ። ***አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፥ ደግሞም። እኔ አባት እሆነዋለሁ*** እርሱም ልጅ ይሆነኛል ያለው ለማን ነው?

**ዕብ 5:5**

እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ ሊቀ ካህናት ሊሆን ራሱን አላከበረም ነገር ግን። አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ያለው እርሱ ነው;

## ኢየሱስና መሲሐዊው ዘመን

ክርስቶስ በምድር ሳለ ያ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይሰጣል የተባለው አዲስ መሲሐዊ ዘመን ፈነጠቀ!

Mark 2:18–22 (AMHB)

18 የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን ይጦሙ ነበር። መጥተውም። የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ
መዛሙርት የሚጦሙት የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጦሙት ስለ ምንድር ነው? አሉት። 19
ኢየሱስም አላቸው። ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሚዜዎች ሊጦሙ ይችላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ
ጋር ሳለ ሊጦሙ አይችሉም። 20 ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፥ በዚያ
ወራትም ይጦማሉ። 21 በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ የሚጥፍ የለም; ቢደረግ ግን፥ አዲሱ መጣፊያ
አሮጌውን ይቦጭቀዋል፥ መቀደዱም የባሰ ይሆናል። 22 በአረጀ አቁማዳም አዲስ የወይን ጠጅ
የሚያኖር የለም; ቢደረግ ግን፥ የወይን ጠጁ አቁማዳውን ያፈነዳል የወይኑም ጠጅ ይፈሳል
አቁማዳውም ይጠፋል አዲሱን የወይን ጠጅ ግን በአዲስ አቁማዳ ያኖራሉ።

Daniel 9:25 (AMHB)

[25] ስለዚህ እወቅ አስተውልም; ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ
አለቃው እስከ መሢሕ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል; እርስዋም በጭንቀት ዘመን
ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች።

ማቴዎስ 1:17–18 (AMHB)

17 እንግዲህ ትውልድ ሁሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት አሥራ አራት ትውልድ፥ ከዳዊትም እስከ ባቢሎን
ምርኮ አሥራ አራት ትውልድ፥ ከባቢሎንም ምርኮ እስከ ክርስቶስ አሥራ አራት ትውልድ ነው። 18
የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ
ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች።

ሞት ከእግሩሥር መረገጥ ጀመረ (ገና ከሙታን ሳይነሳ!); ሐጥያትን ይቅር ማለት ጀመረ(ማር 2:10) (ገና ደሙን ሳያፈስ!); አጋንንት በታላቅ ሐይል እየጮሁ መውጣት ጀመሩ (ገና በመስቀሉ ድል ሳይጎናጸፍ); የፍጥረት ሐይል ለቃሉ መታዘዝ ጀመረ (ማዕበሉን ጸጥ አደረገ; በውሃ ላይ ተራመደ); በትምህርቱና በሐልወቱ የአዲስ ኪዳንን በረከት ሕዝቡ መቅመስ ጀመረ! በዙሪያው 12 ደ/መዛሙርትን መረጦ ሐዋሪያት ብሎ በመሰየም የአዲስ-ኪዳን ሕዝብ መፈጠሩን አመለከተ። 12 የእግዚአብሔር ሕዝብ ሙላትን ያመለክታል; በቀደመው ኪዳን 12 የእስራኤል ነገድ ሕዝቡ እንዲሆን በፋሲካ በግ ደም እንደተዋጀ; አሁን ደግሞ በገዛ ደሙ የሚዋጃቸውን ሕዝብ ገንዘቡ ያደርግ ዘንድ በፋሲካ ራት "ሲበሉም እንካችሁ ይህ ለብዙዎች ሐጥያት የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው!" በማለት ቤተ-ክርስቲያንን መሰረተ (ሐዋ 20)።

Romans 1:1–4 (AMHB)

1-2 ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት
አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ። 3-4 ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ
ተወለደ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ
ተገለጠ ስለ ልጁ ነው; እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ማቴዎስ 28:18–20 (AMHB)

Note.....

a

18 ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። 19-20
እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥
ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው; እነሆም እኔ እስከ
ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

Hebrews 10:12–22 (AMHB) **ንግስና; ክሕነት; መሥዋዕት; አዲስ ኪዳንና መቅደስ**

12 እርሱ ግን ስለ ኃጢአት **አንድን መሥዋዕት** ለዘላለም አቅርቦ **በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፥** 13
ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል። 14 አንድ ጊዜ በማቅረብ
የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና። 15-16 መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ስለዚህ
ይመሰክርልናል; ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ; በልባቸው
ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እጽፈዋለሁ 17 ብሎ ከተናገረ በኋላ፥ ኃጢአታቸውንና ዓመጻቸውንም
ደግሜ አላስብም ይላል። 18 የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ፥ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ
የለም። 19-20 እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ **ወደ ቅድስት
በኢየሱስ ደም በመጋረጃው** ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፥ 21 በእግዚአብሔርም
ቤት ላይ የሆነ **ታላቅ ካህን ስላለን፥** 22 ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም
በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ;

## የልጁ ሁለቱ ምጽዓቶች/ መምጣቶች የዘመን ፍጻሜ መጀመሪያና መደምደሚያ ነው

አሁን የእግዚአብሔር ኪዳናዊ መንግስት በምድር በቤተ-ክርስቲያን አማካይነት ተመስርታለች ነገር ግን ፍጻሜው ግን የነገስታት ንጉስ እስኪመጣ ድረስ ይጠብቃል! በዘልማድ የዘመን መጨረሻ ተብሎ የሚባለው ክርስቶስ ሊመለስ አካባቢ ያለው ዘመንና ሑናቴ ነው። ይህ አስተምሕሮት ግን

### የዲስፐንሴሽናል እንቅስቃሴ አስተምህሮት

ይህ እንቅስቃሴ የጀመረው በ 19ዎቹ ክፍለዘመን መጨረሻ አካባቢ ነው። ይህ እንቅስቃሴ እግዚአብሔር ለቤተክርስቶያንና ለእስራኤል ሁለት የተለያየ አጀንዳ አለው ደግሞም እግዚአብሔር ሑለት ሕዝብ አለው፤ እስራኤልና ቤተክርስቲያን። እነዚህ ሁለቱም ለዘላለም የተለያዩ ሕዝቦች እንደሆኑ ይኖራሉ ባይ ነው። አሁን በተለይ ዛዮኒዝም በመባልና ስለ ትንቢት ፍጻሜ የሚሰጡ አብዛኛዎች ትምህርቶች በዚህ አስተምህሮቶች የተቃኘ ነው። ሆኖም ግን ኤፌሶን 2፡ 11-18 ላይ አይሁድንና አህዛብን በአንድ አካል አስታረቀ እንጂ ለያየ አይልም፡ ለእነርሱም ለእኛም ሰላምን ሰበከልን፣ የቱን እንደምታምኑ ለማወቅ ከፈለጋችሁ፤ ይህ እንደመፈተሻ ሊወሰድ ይችላል፣ “ጦርነት በተነሳ ጊዜ ለእስራኤል ትጸልያላችሁ?” ይህም በፍልስጤም ያሉ ክርስቲያኖች በቦምብ ሲደበደቡ እስራኤል ግን አሁንም የተለየ ሕዝብ ናቸው ማለት ነዋ! ሌላ ኢየሱስ በድብቅ ለቤተክርስቲያን ይመጣል/ መነጠቅ? የመነጠቅ ዓላማው እግዚአብሄር ለአይሁድ ያለውን ፕሮጀክት እንዲቀጥል የአህዛብ ቤተክርስቲያን ትወሰዳለች! እነዚህ ትምህርቶች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ብሉይን ከተጠቀሙበት እጅግ ይለያል።

ይህን ስል ምንም እንኳ ይህ አስተምሕሮት ከቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት የሳተ እንደሆን ብናምንም ነገርግን የሥሕተት ትምህርት ተብሎ ሊመደብ አይገባም። ሁለታችንም በክርስቶስ የምናምን ወንድምና እህቶች እንጂ ጠላቶች አይደለንም። ይህንን ግን ስል የክርስቶስን አዳኛነትና መኮትነት፤ ደግሞም የስሉስ እግዚአብሔርን ዘላለማዊነት የሚክድ አስተምህሮት ግን በአንድ የልዩነት ጎራ አናስቀምጣቸውም።

የዲስፐንሴሽናል እንቅስቃሴ አስተምህሮት ነው።

1 Peter 1:3–5 (AMHB)

3-5 ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ እድፈትም ለሌለበት፥
ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት
ይባረክ; ይህም ርስት **በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ** ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር
ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል።

Note.....

a

1 Peter 1:18–21 (AMHB)

[18-19] ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፥
ነውርና እድፍ እንደ ሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ።
[20-21] ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ፥ ነገር ግን እምነታችሁና ተስፋችሁ በእግዚአብሔር
ይሆን ዘንድ፥ ከሙታን ባስነሣው ክብርንም በሰጠው በእግዚአብሔር በእርሱ ስለምታምኑ ስለ እናንተ
**በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ።**

Hebrews 9:25–28 (AMHB)

[25] ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ፥ ራሱን ብዙ
ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም; [26] እንዲህ ቢሆንስ፥ **ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ** (ἀπὸ
καταβολῆς κόσμου)ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር; አሁን ግን
**በዓለም ፍጻሜ (በዘመናት መጨረሻ)** (ἐπὶ συντελείᾳ τῶν αἰώνων) ራሱን
በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል። [27] ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት
ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፥ [28] እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ፥
የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ፥ ያድናቸው ዘንድ
ለሚጠባበቁት **ሁለተኛ ጊዜ** ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል።

[14-15] ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና። **ዘመኑ
ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች** ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ።

Isaiah 40:1–5 (AMHB)
1 አጽናኑ፥ ሕዝቤን አጽናኑ ይላል አምላካችሁ። 2 ለኢየሩሳሌም ልብ ተናገሩ የተቀጠረችበት ወራት
እንደ ተፈጸመ፥ ኃጢአትዋም እንደ ተሰረየ፥ ከእግዚአብሔርም እጅ ስለ ኃጢአትዋ ሁሉ ሁለት እጥፍ
እንደ ተቀበለች ወደ እርስዋ ጩኹ። 3 የአዋጅ ነጋሪ ቃል። የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ
ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጎዳና በበረሀ አስተካክሉ። 4 ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፥ ተራራውና
ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል; ጠማማውም ይቃናል፥ ስርጓጕጡም ሜዳ ይሆናል; 5
የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፥ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፥ የእግዚአብሔር አፍ ይህን
ተናግሮአልና።...

Isaiah 40:10–12 (AMHB)
10 እነሆ፥ ጌታ እግዚአብሔር እንደ **ኃያል** ይመጣል **ክንዱም** ስለ እርሱ ይገዛል; እነሆ፥ ዋጋው ከእርሱ
ጋር ደመወዙም በፊቱ ነው። 11 መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፥ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ
ይሸከማል፥ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል። 12 ውኆችን በእፍኙ የሰፈረ፥ ሰማይንም በስንዝር
የለካ፥ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ የያዘ፥ ተራሮችን በሚዛን ኮረብቶችንም በሚዛኖች የመዘነ
ማን ነው?...18 እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? ወይስ በምን ምሳሌ
ታስተያዩታላችሁ? 19 የተቀረጸውንስ ምስል ሠራተኛ ሠርቶታል፥ አንጥረኛም በወርቅ ለብጦታል፥
የብሩንም ሰንሰለት አፍስሶለታል። ...25 እንግዲህ እተካከለው ዘንድ በማን መሰላችሁኝ? ይላል
ቅዱሱ። 26 ዓይናችሁን ወደ ላይ አንሥታችሁ ተመልከቱ; እነዚህን የፈጠረ ማን ነው?
ሠራዊታቸውን በቍጥር የሚያወጣ እርሱ ነው፥ ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል; በኃይሉ ብዛትና
በችሎቱ ብርታት አንድስ እንኳ አይታጣውም። 27 ያዕቆብ ሆይ፥ እስራኤልም ሆይ። መንገዴ
ከእግዚአብሔር ተሰውራለች ፍርዴም ከአምላኬ አልፋለች ለምን ትላለህ? ለምንስ እንዲህ ትናገራለህ?
28 አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው;
አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመረመርም። 29 ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፥ ጕልበት
ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል። 30 ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል፥ ጐበዛዝቱም ፈጽሞ
ይወድቃሉ; 31 እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ; እንደ ንስር
በክንፍ ይወጣሉ; ይሮጣሉ፥ አይታክቱም; ይሄዳሉ፥ አይደክሙም።

Isaiah 19:1 (AMHB)

1 ስለ ግብጽ የተነገረ ሸክም። እነሆ፥ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እይበረረ ወደ ግብጽ ይመጣል;
የግብጽም ጣዖታት በፊቱ ይርዳሉ፥ የግብጽም ልብ በውስጥዋ ይቀልጣል።..23 በዚያ ቀን ከግብጽ ወደ

Note.....

a

አሦር መንገድ ይሆናል፥ አሦራዊውም ወደ ግብጽ፥ ግብጻዊውም ወደ አሦር ይገባል; ግብጻውያንም ከአሦራውያን ጋር ይሰግዳሉ። 24-25 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። **ሕዝቤ ግብጽ፥ የእጄም ሥራ አሦር፥ ርስቴም እስራኤል** የተባረከ ይሁን ብሎ ይባርካቸዋልና በዚያ ቀን እስራኤል ለግብጽና ለአሦር ሦስተኛ ይሆናል፥ በምድርም መካከል በረከት ይሆናል።

Isaiah 35:2–10 (AMHB)

የእግዚአብሔርንም ክብር የአምላካችንንም ግርማ ያያሉ። 3 የደከሙትን እጆች አበርቱ፥ የላሉትንም ጕልበቶች አጽኑ። 4 ፈሪ ልብ ላላቸው። እነሆ፥ አምላካችሁ በበቀል በእግዚአብሔርም ብድራት **ይመጣልና፥** መጥቶም ያድናችኋልና በርቱ፥ አትፍሩ በሉአቸው...8 በዚያም ጐዳናና መንገድ ይሆናል እርሱም የተቀደሰ መንገድ ይባላል; ንጹሐንም ያልሆኑ አያልፉበትም፥ ለንጹሐን ግን ይሆናል; ተላላፊዎችና ሰነፎች እንኳ አይስቱበትም። 9 አንበሳም አይኖርበትም፥ ነጣቂ አውሬም አይወጣበትም፥ ከዚያም አይገኙም; የዳኑት ግን በዚያ ይሄዳሉ; 10 እግዚአብሔርም የተቤዣቸው ይመለሳሉ እየዘመሩም ወደ ጽዮን ይመጣሉ; የዘላለም ደስታ በራሳቸው ላይ ይሆናል; ሐሤትንና ደስታን ያገኛሉ፥ ኀዘንና ትካዜም ይሸሻሉ።

Zephaniah 3:14–16 (AMHB)

14 የጽዮን ልጅ ሆይ፥ ዘምሪ; እስራኤል ሆይ፥ እልል በል; የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፥ በፍጹም ልብሽ ሐሤት አድርጊ
ደስም ይበልሽ። 15 እግዚአብሔር ፍርድሽን አስወግዶአል፥ ጠላትሽንም ጥሎአል; የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር
በመካከልሽ አለ፥ ከእንግዲህም ወዲህ ክፉ ነገርን አታዩም። 16 በዚያን ቀን ለኢየሩሳሌም። ጽዮን ሆይ፥ አትፍሪ፥
እጆችሽም አይዛሉ።

Obadiah 21 (AMHB)

21 በዔሳውም ተራራ ላይ ይፈርዱ ዘንድ አዳኞች ወደ ጽዮን ተራራ ላይ ይወጣሉ; መንግሥቱም ለእግዚአብሔር ይሆናል።

Micah 4:1–4 (AMHB)

1 **በመጨረሻውም ዘመን** የእግዚአብሔር ቤት ተራራ በተራሮች ራስ ላይ ጸንቶ ይቆማል፥ ከኮረብቶችም በላይ ከፍ
ከፍ ይላል; አሕዛብም ወደ እርሱ ይጐርፋሉ። 2 ከጽዮን ሕግ፥ ከኢየሩሳሌምም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣልና
ብዙዎች አሕዛብ ሄደው። ኑ፥ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፥ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ; እርሱም መንገዱን
ያስተምረናል፥ በፍለጋውም እንሄዳለን ይላሉ። 3 በብዙዎችም አሕዛብ መካከል ይፈርዳል፥ በሩቅም ባሉ
በብርቱዎች አሕዛብ ላይ ይበይናል; ሰይፋቸውንም ማረሻ፥ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ;
ሕዝብም በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም ከእንግዲህም ወዲህ ሰልፍ አይማሩም። 4 የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር
አፍም ተናግሮአልና ሰው እያንዳንዱ ከወይኑና ከበለሱ በታች ይቀመጣል፥ የሚያስፈራውም የለም።

Isaiah 52:1–2 (AMHB)

1 ጽዮን ሆይ፥ ተነሺ፥ ተነሺ፥ ኃይልሽን ልበሺ; ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ያልተገረዘና ርኩስ
ከእንግዲህ ወዲህ አይገባብሽምና ጌጠኛ ልብስሽን ልበሺ። 2 ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ትቢያን አራግፊ;
ተነሺ፥ ተቀመጪ; ምርኮኛይቱ የጽዮን ልጅ ሆይ፥ የአንገትሽን እስራት ፍቺ።...7 የምስራች የሚናገር፥
ሰላምንም የሚያወራ፥ የመልካምንም ወሬ የምስራች የሚናገር፥ መድኃኒትንም የሚያወራ፥ ጽዮንንም።
አምላክሽ ነግሦአል የሚል ሰው እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው። 8 እነሆ፥ ጕበኞችሽ
ጮኸዋል; እግዚአብሔር ወደ ጽዮን በተመለሰ ጊዜ ዓይን በዓይን ይተያያሉና ድምፃቸውን ያነሣሉ፥
በአንድነትም ይዘምራሉ። 9 እናንተ የኢየሩሳሌም ፍርስራሾች ሆይ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን
አጽናንቶአልና፥ ኢየሩሳሌምንም ታድጎአልና ደስ ይበላችሁ፥ በአንድነትም ዘምሩ።...13 እነሆ፥ ባሪያዬ
በማስተዋል ያደርጋል; ይከብራል ከፍ ከፍም ይላል፥ እጅግ ታላቅም ይሆናል። 14 ፊቱ ከሰዎች ሁሉ
ይልቅ፥ መልኩም ከሰዎች ልጆች ይልቅ ተጐሳቍሎአልና ብዙ ሰዎች ስለ አንተ እንደ ተደነቁ፥ እንዲሁ
ብዙ አሕዛብን ያስደንቃል; 15 ያልተነገረላቸውንም ያያሉና፥ ያልሰሙትንም ያስተውላሉና ነገሥታት
ስለ እርሱ አፋቸውን ይዘጋሉ።

Mark 1:2–4 (AMHB)

2-3 እነሆ፥ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን መንገድ አዘጋጁ
ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ በነቢዩ በኢሳይያስ እንደ ተጻፈ፥

Note.....

a

[4] ዮሐንስ በምድረ በዳ እያጠመቀ የንስሐንም ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት እየሰበከ መጣ...7 ተጎንብሼ
የጫማውን ጠፍር መፍታት የማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ በኋላዩ ይመጣል። 8 እኔ በውኃ
አጠመቅኋችሁ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል እያለ ይሰብክ ነበር።

14-15 ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና። **ዘመኑ
ተፈጸመ** የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ።

Acts 3:21–24 (AMHB)

21 እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው፥ ነገር ሁሉ **እስከሚታደስበት ዘመን
ድረስ ሰማይ ይቀበለው/ይቆይ ዘንድ ይገባልና።** 22 ሙሴም ለአባቶች። ጌታ አምላክ እኔን
እንዳስነሣኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል; በሚነግራችሁ ሁሉ እርሱን ስሙት። 23 ያንም
ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች አለ። 24 ሁለተኛም ከሳሙኤል ጀምሮ
ከእርሱም በኋላ የተናገሩት ነቢያት ሁሉ ደግሞ ስለዚህ ወራት ተናገሩ።

Hebrews 9:6–10 (AMHB)

[6] ይህም እንደዚህ ተዘጋጅቶ ሳለ፥ ካህናት አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ ዘወትር በፊተኛይቱ ድንኳን ይገቡባታል; [7]
በሁለተኛይቱ ግን ሊቀ ካህናት ብቻውን በዓመት አንድ ጊዜ ይገባባታል፥ እርሱም ሰለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ስሕተት
የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ አይገባም; [8] ፊተኛይቱም ድንኳን በዚህ ገና ቆማ ሳለች፥ ወደ ቅድስት የሚወስደው
**መንገድ** ገና እንዳልተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል። [[910|BibleKJV:Heb9:910]] ይህም **ለአሁኑ ዘመን** ምሳሌ ነው፥
እንደዚህም መባና መስዋዕት ይቀርባሉ; እነዚህም **እስከ መታደስ ዘመን ድረስ የተደረጉ፥** ስለ ምግብና ስለ
መጠጥም ስለ ልዩ ልዩ መታጠብም የሚሆኑ የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ ናቸውና የሚያመልከውን በህሊና ፍጹም
ሊያደርጉት አይችሉም።

ልጁ እስኪገለጥ ድረስ በምድር ይሰራ የነበረው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደጥላ ነበር። አሁን ግን የእግዚአብሔር የሐልወቱ መገለጥ በሆነው በእውነተኛው ንጉስ በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት መንግሥቱ ተገልጣለች!

ማቴዎስ 11:12–13 (AMHB)

“12 ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፥ ግፈኞችም
ይናጠቋታል። 13 ነቢያት ሁሉና ሕጉ እስከ ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናገሩ;”

[4] ነገር ግን ***የዘመኑ ፍጻሜ*** በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን **ላከ**;

Ephesians 1:8–10 (AMHB)

8 ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን። 9 በክርስቶስ ለማድረግ እንደ ወደደ እንደ አሳቡ፥
የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና; 10 **በዘመን ፍጻሜ** ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና
በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው።..13 እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፥ ይኸውም
የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ
ቅዱስ ታተማችሁ; 14 እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፥ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ
ድረስ፥ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል።

2 Timothy 1:9–11 (AMHB) [9] ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፥ ይህም
እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም; ይህም ጸጋ ከዘላለም
ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን፥ [10-11] **አሁን ግን** በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ **መገለጥ**
ታይቶአል። እርሱ ሞትን ሽሮአልና እኔ ሰባኪና ሐዋርያ አሕዛብንም አስተማሪ እንድሆን በተሾምሁበት
በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቶአል።

Note.....

a

## የአሁኑና የመጪው ዘመን

ይህ ልጁ የተገለጠበት ዘመን የእግዚአብሔርን ሰዓትና የሰውን ታሪክ በሁለት ዘመናት ከፈለ። ነብያት ይመጣል ብለው የተነበዩት "የጌታ ቀን" ይህም ታላቅ የመዳንና የፍርድ ቀን ደረሰ ነገር ግን አፈጻጸሙ ማንም ባልጠበቀው መንገድ ነው። ይህንን ኢየሱስ የመንግሥተ ሰማያት ሚስጢር ብሎ ያስተማረው ነው። ይህም ሚስጢር የተመሰረተው መንግሥቱ በዚህ ሐጥያት; ሞትና ሰይጣን ይገዙ ዘንድ በተፈቀደላቸው ዘመን ውስጥ መገለጡና ሁለቱም አብረው መቀጠላቸው ነው። ክርስቶስ ግን ሲገለጥ የብረት በትርን ይዞ ሳይሆን; *"ሥጋን አዘጋጀህልኝ እነሆ ፈቃድህን ላደርግ ወረደሁ"* ሳይሆን; ደህነቱን ገልጦ ፍርዱን ግን ማዘግየቱ ይህ አሰራር ክርስቶስነው። አሁን የእግዚአብሔር መንግስት ትሰራለች ነገርግን ልክ አንድ ዘሪ ዘርን እንደሚዘራ ናት። በአንዳንዱ ሕይወት ታፈራለች በሌሎቹ ደግሞ ትናቃለች።

እግዚአብሔር በዘመናት ፍጻሜ ይሆናል ብሎ አስቀድሞ የተናገረው ቀን በሁለት ዘመናት ይከፈላል። ይህም የልጁ ሁለቱ መገለጦች ናቸው።

1. አንድ ታላቅ መዳንን ያስገኝ ዘንድ የሐጥያት መስዋእት ለመሆን ሲሆን;
2. ሁለተኛው ግን የዳግም ምጻቱ ነው! ይህም በእርሱ ለታመኑ ታላቅ የመዳን ቀን; ላላመኑ ደግሞ የፍርድ ቀን ይሆናል!

የልጁ ሁለቱ ምጽዓቶች የብሉይን ተስፋ በሁለት ዘመናት ከፍሎታል! ይህም ""

ማቴዎስ 12:31–32 (AMHB)

31 ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፥ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሰረይለትም። 32 በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል; በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ ***በዚህ ዓለም*** *ቢሆን ወይም* ***በሚመጣው*** አይሰረይለትም።

Mark 10:29–30 (AMHB)

29 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ። እውነት እላችኋለሁ፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ፥ 30 አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንና እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም።

Luke 20:34–36 (AMHB)

34 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። **የዚህ ዓለም** ልጆች ያገባሉ ይጋባሉም፥ 35 ያን ዓለምና ከሙታን ትንሣኤ ሊያገኙ የሚገባቸው እነዚያ ግን አያገቡም አይጋቡምም፥ እንደ መላእክት ናቸውና፥ 36 ሊሞቱም ወደ ፊት አይቻላቸውም፥ የትንሣኤም ልጆች ስለ ሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።

Matthew 13:36–43 (AMHB)

36 በዚያን ጊዜ ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ። ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው። የእርሻውን እንክርዳድ ምሳሌ ተርጕምልን አሉት። 37 እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው። መልካምን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው; **እርሻውም ዓለም (ይህ ዘመን-αἰῶνος) ነው**; 38 መልካሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው; 39 እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፥ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው; **መከሩም የዓለም (የዘመን) መጨረሻ ነው፥** አጫጆችም መላእክት ናቸው። 40 እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል፥ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል። 41 የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፥ 42 ወደ እቶነ እሳትም ይጥሉአቸዋል; በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። 43 በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።

Matthew 24:3 (AMHB)

Note.....

a

3 እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው። ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና **የዘመን (ዓለም) መጨረሻ** ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት።

Hebrews 6:4–6 (AMHB)

4 አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን 5 መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና **ሊመጣ ያለውን የዓለም (ዘመን) ኃይል የቀመሱትን** 6 በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው; ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና ያዋርዱትማልና።

Ephesians 1:20–23 (AMHB)

20-21 ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና **በዚህ ዓለም ብቻ** ሳይሆን **ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ** ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል;  22 ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው።  23 እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት።

Ephesians 2:1–2; 5-7

1-2 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ; በእነርሱም፥ *በዚህ ዓለም* እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።...5 ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፥  6-7 በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ፥ ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።

Galatians 1:4–5 (AMHB)

4 ክፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለ ኃጢአታችን ራሱን ሰጠ።  5 ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን; አሜን።

1 Corinthians 10:9–11 (AMHB)

9 ከእነርሱም አንዳንዶቹ ጌታን እንደ ተፈታተኑት በእባቦቹም እንደ ጠፉ ጌታን አንፈታተን።  10 ከእነርሱም አንዳንዶቹ እንዳንጎራጎሩ በሚያጠፋውም እንደ ጠፉ አታንጐርጕሩ።  11 ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፥ እኛንም **የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥጸን ተጻፈ።**

1 Corinthians 15:23–28 (AMHB)

23 ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል; ክርስቶስ እንደ በኵራት ነው፥ በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው;  24 በኋላም፥ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ፥ **ፍጻሜ ይሆናል።**  25 ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና።  26 የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው;  27 ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቶአልና። ነገር ግን። ሁሉ ተገዝቶአል ሲል፥ ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆኑ ግልጥ ነው።  28 ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል።

ስለዚህ አዲስ ኪዳን በሁለት ዘመናት መጋጠሚያ ላይ ያለን ሕዝቦች ነን። ስለዚህ መስቀልና ትንሳኤ; ድካምና ብርታት; ክብርና ውርደት; ለቅሶና መጽናናት ሁለቱም እውነቶች ናቸው። አሮጌው እያለፈ አዲሱ እየፈነጠቀ ነውና!

በዚህ በአሁኑ ዘመን ከብዶብን ተስፋችን እንናፍቃለን። ምንም እንኳ የመንፈስን ሕይወት ብንቀበልም ነገርግን ሞች ሰውነታችን ግን በትንሳኤ እስኪለወጥ ሞት በእኛ እየሰራ ነው (ፊል 2፡ );

Philippians 3:20–21 (AMHB)

Note.....

a

20 እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ
ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤ 21 እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር፥
ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል።

Romans 8:18–28 (AMHB)

18 ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን **የአሁኑ ዘመን** ሥቃይ ምንም እንዳይደለ
አስባለሁ። 19 የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና። 20 ፍጥረት
ለከንቱነት ተገዝቶአልና፥ በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤ 21 ተስፋውም
ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት
እንዲደርስ ነው። 22 ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን
እናውቃለንና። 23 እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ
የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን። 24
በተስፋ ድነናልና፤ ነገር ግን ተስፋ የሚደረግበቱ ነገር ቢታይ ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን
ተስፋ ያደርገዋል? 25 የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግሥት እንጠባበቃለን። 26
እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥
ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ 27 ልብንም የሚመረምረው
የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።
28 እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ
እናውቃለን።

2 Corinthians 5:1–5 (AMHB)

1 ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፥ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት
የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለንና። 2 በዚህ ውስጥ በእውነት
እንቃትታለንና፥ 3 ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና ለብሰን
ራቁታችንን አንገኝም። 4 በእውነትም የሚሞተው በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ
ልንገፈፍ የማንወድ ስለ ሆነ፥ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብዶን እንቃትታለን። 5 ነገር ግን ለዚሁ
የሠራን እግዚአብሔር ነው እርሱም የመንፈሱን መያዣ ሰጠን።

የመጨረሻው ጠላታችን ሞት ነው!

Romans 8:9–10 (AMHB)

9 እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም።
የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም። 10 ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን
ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፥ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው።

The body is dead because of sin: because of the sin of Adam curse of death is working in our body. We are dying each day as a result. However at the same time the Spirit is life (parallel with the body is dead) because of the one righteous act of Christ, the reassurection power of Christ is at work in us through his Spirit. Life is the characteristic of the age to come where as death is the chief characteristic of the present evil age that is under God's judgement. In summary:- if Christ is in you, on one hand your body is subject to death (NIV) because of the present evil age and on the other hand the life of the age to come (life after the reassurection) is at the same time is working Now in this mortal body. Therefore there is a constant tension between the Sin tainted present evil age (the flesh) and the life giving principle of the age to come coming already in the present (the Spirit).

## ሠሰን-መጠቅ ጌትነት (Universal Kingdom) እና የኪዳን ጌትነት

**የእግዚአብሔር ገዢነቱ፤ ንግሥናው ሥልጣኑና መንግስቱ የተመሰረቱት *በፈጣሪነቱ* ነው።
እነዚህም ፍጥረታት ለክብሩ-መገለጫ ይሆኑ ዘንድ በነጻ ፈቅዶ የፈጠራቸው የእጆቹ ሥራዎች
ናቸው።**

Note.....

a

ምሳሌ፡ አራቱ እንሥሣት ፍጥረትን ወክለው (ወሰን-መጠቅ ጌትነት) እንደዚሁም ደግሞ 24ቱ ሽማግሌዎች የተዋጁትን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወክለው (የኪዳን ጌትነት) ሲያመሰግኑ ይታያሉ። ራዕ 4:10-11)

በነዚህ ሁለቱ ዓይነት አገዛዞ የተጎናጸፋቸው ስሞቹ፡ *"ኤል; ኤሎሂም"*-የሁሉ ጌትነቱን ሲያንጸባርቅ; *"ያህ-ያህዌ"* የተባለው የግል-የህላዌ ስሙ ደግሞ ኪዳናዊ/ ታዳጊ አገዛዙን ይገልጣል!

a. **ምጡቅ-ፈጣሪነቱ፡** ይህም ዓለምት በቃሉ እንደ ተዘጋጁ፥ ሁሉንም ነገር ካለመኖር ወደመኖር ያመጣና የሚታየው ነገር ሁሉ በማይታየው በእርሱ መፈጠራቸው ነው። ይህንን ክብር በላቲን "creatio ex nihilo ("creation out of nothing"; ከባዶ ውስጥ የወጣ ፍጥረት)"

- Genesis 1:31 "እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ ስድስተኛ ቀን።"

b. **ምጡቅ ሕያውነቱ፡-** በራሱ ሕያው የሆነና ምሉዕ የሆነው አምላክ ለፍጥረቱ ሁሉ እስትንፋስ መሰረት መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የፍጥረቱ ገዢ እንዲሆን እንዳደረገው ይናገራል፡

- ."..10 እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው; እርሱም ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው;"

- Deuteronomy 5:26 "ከሥጋ ለባሽ ሁሉ እኛ እንደ ሰማን በእሳት ውስጥ ሆኖ ሲናገር *የሕያው አምላክን* ድምፅ ሰምቶ በሕይወቱ የኖረ ማን ነው?

- Ps 42፡2 ነፍሴ ወደ *ሕያው አምላክ* ተጠማች; መቼ እደርሳለሁ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ?

## c. ለአግዚአብሔር የጌትነት መሰረት ፈጣሪነቱና ሕያውነቱ ስለመሆኑ የተሰጠ ሐቲት

- Genesis 14:19 የልዑል እግዚአብሔር ካህን የነበረው የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም...እንዲህ ሲል ባረከው; **ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ልዑል አምላክ** (**ኤል-ኤልዮን**) አብራምን ይባርክ; ጠላቶችህን አሳልፎ በእጅህ የሰጠህ **ልዑል አምላክ** (**ኤል-ኤልዮን**) **ይባረክ።**

- Genesis 14:22–24 አብራምም የሰዶምን ንጉሥ አለው። **ሰማይንና ምድርን ወደሚገዛ ወደ ልዑል አምላክ** (**ኤል-ኤልዮን**) **እጄን ከፍ አድርጌአለሁ**; አንተ አብራምን ባለጠጋ አደረግሁት እንዳትል፥ ብላቴኖቹ ከበሉት በቀር ከእኔ ጋር ከሄዱትም ድርሻ በቀር፥ ፈትልም ቢሆን የጫማ ማዘቢያም ቢሆን፥ ለአንተ ከሆነው ሁሉ እንዳልወስድ; አውናን ኤስኮልም መምሬም እነርሱ ድርሻቸውን ይውሰዱ።

- Exodus 20:8–11 የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። 9 ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ; 10 ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው; ....11 እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ***ዐርፎአልና;*** ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም።
    - o *የእግዚአብሔር እረፍት በፈጠረው ሁሉ ላይ መንገሱን ያሳያል* Genesis 1:31 - 2:1–3 "እግዚአብሔርም **ያደረገውን ሁሉ አየ፥** እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ ስድስተኛ ቀን። "ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ **ተፈጸሙ።** 2 እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ; በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። 3 እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን **ባረከው** ቀደሰውም; እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና።"
    - o *የመገንኛው ድንኳን ሥራ በፍጥረት ሥራ ተመስሏል፡ "Exodus 39:42–43* "እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘ ሁሉ እንዲሁ የእስራኤል ልጆች ሥራውን ሁሉ ሠሩ። 43 ሙሴም ***ሥራውን ሁሉ አየ፥*** እነሆም አድርገውት ነበር; እግዚአብሔር እንዳዘዘው እንዲሁ አድርገውት ነበር; **ሙሴም ባረካቸው።**
    - o *እግዚአብሔር ከመገንኛው ድንኳን ሆኖ ሕዝቡን ይመራል፡* Exodus 40:33–38 (AMHB) በማደሪያውና በመሠዊያውም ዙሪያ አደባባዩን ተከለ; የአደባባዩንም ደጃፍ መጋረጃ ዘረጋ። እንዲሁም ሙሴ ሥራውን ፈጸመ። 34 ደመናውም የመገናኛውን ድንኳን ከደነ፥ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ። 35 ደመናውም በላዩ ስለ ነበረ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ስለ ሞላ ሙሴ ወደ መገናኛው ድንኳን ይገባ ዘንድ አልቻለም። 36 ደመናውም ከማደሪያው በተነሣ ጊዜ የእስራኤል ልጆች በመንገዳቸው ሁሉ ይጓዙ ነበር። 37 ደመናው ባይነሣ እስከሚነሣበት ቀን ድረስ አይጓዙም ነበር። 38

Note.....

a

በመንገዳቸውም ሁሉ በእስራኤል ቤት ሁሉ ፊት የእግዚአብሔር ደመና በማደሪያው ላይ በቀን ነበረና፥ እሳትም በሌሊት በዚያ ላይ ነበረና።

- *ሰለሞን ቤተመቅደሱን **በሰባት ዓመት** ሰርቶ ጨረሰ (1ነገ 6:38); የተመረቀው **በሰባተኛው** ወርና **ለሰባት** ቀን በሚከበር በዳስ በዓል ነው* (እግዚአብሔር ከስራው በሰባት ቀን እንዳረፈ እንደዚሁም በሕዝቡ መካከል የመንግሥቱ መገለጫ የሆነው የቤተ-መቅደሱም ሥራ በሥነ ፍጥረት ሥራ መመሰሉን ሲያሳይ በሰባት ዓመት ሥራው ተጠናቀቀ ):
    - 1 Kings 8:10–43 "ካህናቱም ከመቅደሱ በመጡ ጊዜ ደመናው የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው። 11 **የእግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶ ነበርና ካህናቱ ከደመናው የተነሣ ለማገልገል ይቆሙ ዘንድ አልቻሉም።** 12 ሰሎሞንም። እግዚአብሔር። በጨለማው ውስጥ እኖራለሁ ብሎአል; 13 እኔም ለዘላለም የምትኖርበት ማደሪያ ቤት በእውነት ሠራሁልህ አለ። **በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን**? [ምጡቅነቱ] እነሆ፥ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም; ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ! ነገር ግን፥ አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ ወደ ባሪያህ ጸሎትና ልመና ተመልከት፥ ዛሬም ባሪያህ በፊትህ የሚጸልየውን ጸሎትና ጥሪውን ስማ;...41–43 ከሕዝብህም ከእስራኤል ወገን ያልሆነ እንግዳ ታላቁን ስምህን፥ ብርቱይቱንም እጅህን፥ የተዘረጋውንም ክንድህን ሰምቶ ስለ ስምህ ከሩቅ አገር በመጣ ጊዜ፥ መጥቶም ወደዚህ ቤት በጸለየ ጊዜ፥ 43 አንተ በማደሪያህ በሰማይ ስማ; **የምድርም አሕዛብ ሁሉ ስምህን ያውቁ ዘንድ እንደ ሕዝብህም እንደ እስራኤል ይፈሩህ ዘንድ**፥ በዚህም በሠራሁት ቤት ስምህ እንደተጠራ ያውቁ ዘንድ፥ እንግዳው የሚለምንህን ሁሉ አድርግ።
- *እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን እንድረፈ በመቅደሱ ሥፍራ በጽዮን አርፏል፡* "Psalm 132:7–8 ወደ ማደሪያው እንግባ; እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንስገድ 8 እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ አንተና የሐይልህ ታቦት ወደ ማረፊያ ሥፍራ ሂዱ...13እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና; ማደሪያውም ትሆን ዘንድ ወዷልና እንዲህ አለ፡ ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት; ፈልጌያታለሁና በእርሷ እኖራለሁ!"
- *እግዚአብሔር ሕዝቡን ከባርነት ቤት አውጥቶ እየመራ የወሰዳቸው ወደ ክብሩ ማደሪያሥፍራ ነበር። ሕዝቡን ገንዘቡ ያደርግ ዘንድ የገለጠው ክብርና ህያው ስም (ያህዌ) መንግስቱን ገለጠ Exodus 15: 11–14* "አቤቱ፥ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው? በምስጋና የተፈራህ፥ ድንቅንም የምታደርግ፥ በቅድስና የከበረ እንደ አንተ ያለ ማን ነው? 12 ቀኝህን ዘረጋህ፥ ምድርም ዋጠቻቸው። **13 በቸርነትህ የተቤዠሃቸውን ሕዝብህን *መራህ;*** (ኪዳናዊ ጌትነት) በኃይልህ ወደ ቅዱስ *ማደሪያህ አገባሃቸው።* 14 አሕዛብ ሰሙ፥ ተንቀጠቀጡም; በፍልስጥኤም የሚኖሩትን ምጥ ያዛቸው። 15 የዚያን ጊዜ የኤዶም አለቆች ደነገጡ; የሞአብን ኃያላን መንቀጥቀጥ ያዛቸው; በከነዓን የሚኖሩ ሁሉ ቀለጡ። 16 አቤቱ፥ ሕዝብህ እስኪያልፍ ድረስ፥ የተቤዠኸው ሕዝብ እስኪያልፍ ድረስ፥ ፍርሃትና ድንጋጤ ወደቀባቸው; በክንድህ ብርታት እንደ ድንጋይ ዝም አሉ። 17 አቤቱ፥ አንተ ታስገባቸዋለህ፥ በርስትህ ተራራም ትተክላቸዋለህ፥ አቤቱ፥ **ማደሪያህ ባደረግኸው ስፍራ፥ አቤቱ፥ እጆችህ ባዘጋጁት መቅደስ። 18 እግዚአብሔር ለዘላለሙ እስከ ፍጻሜ ይነግሣል።**
- Jeremiah 10:1–7 (AMHB)
    - 1 እናንተ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ እግዚአብሔር በእናንተ ላይ የተናገረውን ቃል ስሙ። 2 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የአሕዛብን መንገድ አትማሩ ከሰማይ ምልክትም አትፍሩ; አሕዛብ ይፈሩታልና። 3 የአሕዛብ ልማድ ከንቱ ነውና; ዛፍ ከዱር ይቈረጣል፥ በሠራተኛም እንጅ በመጥረቢያ ይሠራል። 4 በብርና በወርቅ ያስጌጡታል፥ እንዳይናወጥም በችንካርና በመዶሻ ይቸነክሩታል። 5 እንደ ተቀረጸ ዓምድ ናቸው እነርሱም አይናገሩም; መራመድም አይቻላቸውማን ይሸከሙአቸዋል። ክፉ መሥራትም አይቻላቸውምና፥ ደግምም መልካም ይሠሩ ዘንድ አይችሉምና አትፍሩአቸው። 6 አቤቱ፥ እንደ አንተ ያለ የለም; አንተ ታላቅ ነህ ስምህም በኃይል ታላቅ ነው። 7 የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ በአሕዛብ ጥበበኞች ሁሉ መካከል በመንግሥታቸውም ሁሉ እንደ አንተ ያለ ስለሌለ፥ አንተን መፍራት ይገባልና አንተን የማይፈራ ማን ነው?

      **...10 እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው; እርሱም ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው**; ከቍጣው የተነሣ ምድር ትንቀጠቀጣለች; አሕዛብም መዓቱን አይችሉም። 11 **እናንተም። ሰማይንና ምድርን ያልፈጠሩ እነዚህ አማልክት ከምድር ላይ ከሰማይም በታች ይጠፉሉ ትሉአቸዋላችሁ።** 12 **ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፥ ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው።** 13 ድምፁን ባሰማ ጊዜ ውኆች በሰማይ ይሰበሰባሉ፥ ከምድርም ዳር ደመናትን ከፍ ያደርጋል; ለዝናቡም መብረቅን ያደርጋል፥

Note.....

a

ነፋስንም ከቤተ መዛግብቱ ያወጣል።  14 ሰው ሁሉ እውቀት አጥቶ ሰንፎአል፥
አንጥረኛም ሁሉ ከቀረጸው ምስል የተነሣ አፍሮአል; ቀልጦ የተሠራ ምስሉ
ውሸት ነውና፥ እስትንፋስም የላቸውምና።  15 እነርሱ ምናምንቴና የቀልድ
ሥራ ናቸው; በተጐበኙ ጊዜ ይጠፋሉ።  **16 የያዕቆብ እድል ፈንታ እንደ እነዚህ
አይደለም; እርሱ የሁሉ ፈጣሪ ነውና; እስራኤልም የርስቱ ነገድ ነውና; ስሙ
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው።**

o ***ሥለዚህ የእግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጥሮ ማረፉ የመንግሥቱ ክብር መንሰራፋቱን ያመለክታል***

- 2 Kings 19:14-15 “ሕዝቅያስም (የአሦር ንጉስ የጻፈውን ደብዳቤውን) ከመልእክተኞች እጅ ተቀብሎ
አነበበው; ሕዝቅያስም ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጥቶ በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው።  ሕዝቅያስም
ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ጸለየ። **በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ የእስራኤል አምላክ አቤቱ፥ አንተ
ብቻህን የምድር ነገሥታት ሁሉ አምላክ ነህ; ሰማይንና ምድርን ፈጥረሃልና።**16 አቤቱ፥ ጆሮህን
አዘንብልና ስማ; አቤቱ፥ ዓይንህን ክፈትና እይ; በሕያው አምላክ ላይ ይገዳደር ዘንድየላከውን
የሰናክሬምን ቃል ስማ።  17 አቤቱ፥ በእውነት የአሦር ነገሥታት አሕዛብንና ምድራቸውን አፍርሰዋል፥
18 አማልክቶቻቸውንም በእሳት ላይ ጥለዋል; የእንጨትና የድንጋይ የሰው እጅ ሥራ ነበሩ እንጂ
አማልክት አልነበሩምና; ስለዚህ አጥፍተዋቸዋል።  19 እንግዲህም አምላካችን አቤቱ፥ የምድር
መንግሥታት ሁሉ አንተ ብቻ እግዚአብሔር አምላክ እንደ ሆንህ ያውቁ ዘንድ ከእጁ እንድታድነን
እለምንሃለሁ።  20 የአሞጽም ልጅ ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ ወደ ሕዝቅያስ ላካ። የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ስለ አሦር ንጉሥ ስለ ሰናክሬም ወደ እኔ የለመንኸውን ሰምቻለሁ።  21
እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የተናገረው ቃል ይህ ነው። ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ ቀላል አድርጋሃለች፥
በንቀትም ስቃብሃለች; የኢየሩሳሌም ልጅ በላይህ ራስዋን ነቅንቃብሃለች።  22 የተገዳደርኸው፥
የሰደብኸውስ ማን ነው? ቃልህንስ ከፍ ከፍ ያደረግኸው ዓይንህንም ወደ ላይ ያነሣኸው በማን ላይ
ነው? በእስራኤል ቅዱስ ላይ ነው።  23 አንተስ። በሰረገላዬ ብዛት ወደ ተራሮች ከፍታ፥ ወደ ሊባኖስ
ጥግ ላይ ወጥቻለሁ; ረጃጅሞቹንም ዝግባዎች የተመረጡትንም ጥዶች እቈርጣለሁ፥ ወደ አገሩም
ዳርቻና ወደ ቀርሜሎስ ዱር እገባለሁ።  24 ቈፈርሁም፥ እንግዳውንም ውኃ ጠጣሁ; የተገደበውንም
ውኃ ሁሉ በእግሬ ጫማ አደርቃለሁ ብለህ በመልእክተኞችህ እጅ በእግዚአብሔር ላይ ተገዳደርህ።
25 እኔ ጥንቱን እንደ ሠራሁት፥ ቀድሞውንም እንዳደረግሁት አልሰማህምን? አሁንም የተመሸጉትን
ከተሞች የፍርስራሽ ክምር እስኪሆኑ ድረስ እንድታፈርስ አደረግሁህ።  26 ስለዚህም የሚኖሩባቸው
ሰዎች እጃቸው ዝሎአል፥ ደንግጠውም ታውከዋል; እንደ ምድረ በዳ ሣር፥ እንደ ለምለምም ቡቃያ፥
በሰገነትም ላይ እንዳለ ሣር፥ ሳይሸት ዋግ እንደ መታውም እህል ሆነዋል።  27 እኔ ግን መቀመጫህንና
መውጫህንም መግቢያህንም፥ በእኔም ላይ የተቈጣኸውን ቍጣ አውቄአለሁ።  28 ቍጣህና
ትዕቢትህ ወደ ጆሮዬ ደርሶአልና ስለዚህ ስናጋዬን በአፍንጫህ፥ ልጓሜንም በከንፈርህ አደርጋለሁ፥
በመጣህበትም መንገድ እመልስሃለሁ።

- Psalm 96:4–10 (AMHB) 4 እግዚአብሔር ታላቅ ምስጋናውም ብዙ ነውና፥ በአማልክትም ሁሉ ላይ
የተፈራ ነውና። 5 የአሕዛብ አማልክት ሁሉ አጋንንት ናቸውና; **እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ።** 6 ...
7 የአሕዛብ ወገኖች፥ ለእግዚአብሔር አምጡ፥ ክብርና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አምጡ; 8 ለስሙ
የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ; ቍርባን ያዙ ወደ አደባባዮችም ግቡ። 9 በቅድስናው ስፍራ
ለእግዚአብሔር ስገዱ; ምድር ሁሉ በፊቱ ትነዋወጥ። 10 **በአሕዛብ መካከል። እግዚአብሔር ነገሠ በሉ።**
እንዳይናወጥም ዓለሙን እርሱ አጸናው፥ አሕዛብንም በቅንነት ይፈርዳል።

- Isaiah 42:5–8 *"ሰማያትን የፈጠረ የዘረጋቸውም፥ ምድርንና በውስጥዋ ያለውን ያጸና፥ በእርስዋ ላይ
ለሚኖሩ ሕዝብ እስትንፋስን፥ ለሚሄዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል። እኔ እግዚአብሔር በጽድቅ ጠርቼሃለሁ፥ እጅህንም እይዛለሁ እጠብቅህማለሁ፥ የዕውሩንም
ዓይን ትከፍት ዘንድ የተጋዘውንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ
ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን አድርጌ እሰጥሃለሁ።  8 እኔ እግዚአብሔር ነኝ; ስሜ ይህ
ነው; ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም።*

- Is 40: 12–28

- Isaiah 44:24

  ከማኅፀን የሠራህ፥ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ። ሁሉን የፈጠርሁ፥ ሰማያትን ለብቻዬ
  የዘረጋሁ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ; ከእኔ ጋር ማን ነበረ?

- Isaiah 45:5–8

  እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም ሌላ ማንም የለም; ከእኔም በቀር አምላክ የለም; በፀሐይ መውጫና
  በምዕራብ ያሉ ከእኔ በቀር ማንም ሌላ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ አስታጠቅሁህ፥ አንተ ግን
  አላወቅኸኝም...7 ብርሃንን ሠራሁ፥ ጨለማውንም ፈጠርሁ; ደኅንነትን እሠራለሁ፥ ክፉትንም
  እፈጥራለሁ; እነነዚህን ሁሉ ያደረግሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ።  8 እናንተ ሰማያት ከላይ አንጠባጥቡ
  ደመናትም ጽድቅን ያዝንቡ; ምድርም ትከፈት መድኃኒትንም ታብቅል፥ ጽድቅም በአንድነት ይብቀል;

Note.....

a

እኔ እግዚአብሔር ፈጥሬዋለሁ። 9 ከሠሪው ጋር ለሚታገል ወዮለት! በምድር ሸክላዎች መካከል ያለ ሸክላ ነው። ጭቃ ሠሪውን። ምን ትሠራለህ? ወይስ ሥራህ። እጅ የለውም ይላልን? 10 አባትን። ምን ወልደሃል? ወይም ሴትን። ምን አማጥሽ? ለሚል ወዮ….21 ይናገሩ ይቅረቡም በአንድነትም ይማከሩ; ከጥንቱ ይህን ያሳየ ከቀድሞስ የተናገረ ማን ነው? ያሳየሁም የተናገርሁም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም; እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ፥ ከእኔም በቀር ማንም የለም። 22 እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ፥ እኔ አምላክ ነኝና፥ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ። 23 ቃሌ ከአፌ በጽድቅ ወጥታለች፥ አትመለስም። ጒልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፥ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ።

## የመንግሥት፡ ሁለት፡ ገጽታዎች በአስተርጓሚ እይታ

እግዚአብሔር ፍጥረትን ሲፈጥር ፍጹም ፍጥረት ባይሆንም ነገር ግን ሁሉም መልካም እንደሆን አየ። ከላይ እንደተመለከትነውም በሰባተኛው ቀን አረፈ!

### የእግዚአብሔር መንግሥትና ፍጥረት

- ሰውንም እንደ አምሳሉ በመፍጠር በፈጠርው ነገር ላይ ሾመው/እንደራሴነት **የንግሥና ሹመት።** ይህ ባለቤትነትን ሳይሆን ኃላፊነት ነው; ይህ ሹመት *"ባረካቸው"* በሚለው ዋነኛ ቃል ተገልጧል!

  **Genesis 1:26–28**

  26 እግዚአብሔርም አለ። ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር; የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።
  27 እግዚአብሔርም ሰውን **በመልኩ ፈጠረ;**
  በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው;
  ***ወንድና ሴት አድርጎ*** ፈጠራቸው።
  28 እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው።
  ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም;
  የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች
  በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ *ግዙአቸው።*

- "አምሳል" - በጥንታዌው ቅርብ ምስራቅ ባህልና ወግ ነገስታት በግዛታቸው በተወሰኑ አዋሳኝ ክልሎች ላይ የገዛ-ምስሎቻቸውን ያኖራሉ። ይህም ድሪዎቹና እንግዶች የዚህ የረገጡት ምድር ገዢ ማን እንደሆን ገላጭ ነው።

- ስለዚህ ሰው የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆኖ ፍጥረትን በጽድቅና በፍትህ እንዲያስተዳድር በስድስተኛው ቀን "በአምሳሉ" ፈጠረው።

  - ***ማንጸባረቅ፡-*** በጽድቅ; በቅድስና በእውቀት እግዚአብሔርን ማንጸባረቁ (Eph. 4:24; Col. 3:10)
  - ***መግዛት፡*** የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ***ይግዙ*** (ዘፍ 9:2; Ps 8:6–8; ያዕ 3:7)
  - **የእርስበእርስ ግንኙነት፡** ***ወንድና ሴት አድርጎ*** ፈጠራቸው።

- ነገር ግን ይህን ሹመትና ሃላፊነት የሚወጣው የእግዚአብሔርን ወሰን-መጠቅ ሥልጣኑን በምትገልጠው በኤደን ገነት መካከል ባለችው ዛፍ ተምሳሌትነት ለተሰጠው ትዕዛዝ ሲገዛ ብቻ ነው። ይህም **የክህነት ሥራው** ነበር።

  - ኤደን የሥልጣን ሥፍራ ናት ዛፉም የእግዚአብሔርን የሥልጣን ትእዛዝ/ መንግሥት ትወክላለች። ይህ ፍጥረት ጌታ አለው; ጌታውም ሰው አይደለም።

    - 8 እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ በዔድን ገነትን ተከለየፈጠረውንም ሰው ከዚያው አኖረው።….16 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው። ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ; 17 ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ; ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን **ትሞታለህና።**

Note…..

a

- ኤደን የእግዚአብሔር ሕላዌ የሚገለጥባት የመቅደስ ምሳሌ ናት
    - Genesis 3:8 እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ
- የአዳም በኤደን ገነት የተሰጠው *ሥራ* የንግ*ሥ*ና *ሥራ* ሳይሆን የክህነት *ሥራ* ነበር;
    - Genesis 2:15 (AMHB) አራተኛውም ወንዝ ኤፍራጥስ ነው። እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው።

## የእግዚአብሔር መንግሥትና የሰው ውድቀት

1) መልካምና ክፉውን የምታሳውቀው ዛፍ የንጉስ ፍርድ ምሳሌ ናት። በጥንታዌው ቅርብ ምስራቅ ባህልና ወግ (Ancient Near East History) መሰረት የዛፍ “የፍርድ ቤት” ምልክት ነበር። ይህ አሁን የሚዛን ምልክት እንደሆነው ማለት ሲሆን በተለይ በአንዳንድ ባሕል (ለምሳሌ በኦሮምያ ሰንደቅ-ዓላማ) ላይ አሁንምም ይህ ምልክት ይገኛል።
    a) **1 ነገ 3: 7–14** አሁንም፥ አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ እኔን ባሪያህን በአባቴ በዳዊት ፋንታ አንግሠኸኛል;
    እኔም መውጫንና መግቢያን የማላውቅ ታናሽ ብላቴና ነኝ። 8 ባሪያህም ያለው አንተ በመረጥኸው
    ሕዝብህ ስለ ብዛቱም ይቈጠርና ይመጠን ዘንድ በማይቻል በታላቅ ሕዝብ መካከል ነው። 9
    ስለዚህም በሕዝብህ ላይ **መፍረድ** ይችል ዘንድ፥ መልካሙንና ክፉውንም **ይለይ ዘንድ** ለባሪያህ
    አስተዋይ ልቡና ስጠው; አለዚያማ በዚህ በታላቅ ሕዝብህ ላይ ይፈድ ዘንድ ማን ይችላል? 10
    ሰሎሞንም ይህን ነገር ስለ ለመነ፥ ነገሩ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው። 11 እግዚአብሔርም አለው።
    ፍርድን ትለይ ዘንድ ለራስህ ማስተዋልን ለመንህ እንጂ ለራስህ ብዙ ዘመናትን ባለጠግነትንም
    የጠላቶችህንም ነፍስ ሳትለምን ይህን ነገር ለምነሃልና እነሆ፥ 12 እኔ እንደ ቃል አድርጌልሃለሁ; እነሆ፥
    ማንም የሚመስልህ ከአንተ በፊት እንደሌለ ከአንተም በኋላ እንዳይነሣ አድርጌ ጥበበኛና አስተዋይ
    ልቡና ሰጥቼሃለሁ። 13 ደግሞም ከነገሥታት የሚመስልህ ማንም እንዳይኖር ያልለመንኸውን
    ባለጠግነትና ክብር ሰጥቼሃለሁ። 14 አባትህም ዳዊት እንደ ሄደ፥ ሥርዓቴንና ትእዛዜን ትጠብቅ ዘንድ
    በመንገዴ የሄድህ እንደ ሆነ፥ ዕድሜህን አረዝመዋለሁ።
    b) ይህ የንጉስ ክብር ባህሪያቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ፍርድ; ጥበብና ፍትህ ናቸው። ቅን ፍርድ ማለት ክፉውንና መልካሙን መለየት ማለት ነው! ለምሳሌ (ኢሳ 7:15; ዕብ 5:14) እነዚህ ኋላ በዳዊት እግር ተተክቶ የሚነግሰው የመሲሁ የንግሥና ባህሪያቶች ናቸው “ታማኝነት; ቅን ፍርድ; ጥበብ”; እነዚህ የአዲስ ኪዳን የመንግስት ልጆች ባህሪያቶች ይሆኑ ዘንድ ተሰጥተዋል
2) ሴቲቱ የእባቡን ምክር ሰምታ እግዚአብሔር በለየላቸው ፍርድ መኖር ትተው የራሳቸውን ፍርድ ፈለጉ። ይህ በንጉሱ በእግዚአብሔር ላይ የመንግሥት ግልበጣ አመጽ ነው።
    a) Genesis 3:4–6 እባብም ለሴቲቱ አላት። ሞትን አትሞቱም; 5 ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ። 6 ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች; ከፍሬውም ወሰደችና በላች; ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ።
    b) ሐጥያት ዓመጽ ነው! ሰው ከሰይጣን ጋር በመተባበር አንድ ሆነ!
3) እግዚአብሔርም፡- ተገለጠ (ድምጹን ሰሙ) ፈረደ! ውጤቱም እርግማን ነበር; እግዚአብሔር ግን በፍርዱ ውስጥ ጸጋ ገለጠ፡
    a) የእባቡ መርገም “Genesis 3:15 “በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ; እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።”
    b) *“በዘርህና በዘርዋም መካከል፥ ጠላትነትን አደርጋለሁ!”* ይህ የሁለቱ አገዛዝ መጀመሪያ ነው። እግዚአብሔር በነዚህ በአመጹት ጠላቶቹ ላይ ጌታ መሆኑን በፍርዱ አሳይቷል! ነገር ግን ፍጻሜ መሆን ሲችል ፍርዱን አዘገየ! በፈንታው ሁለት ዘር እንዲበቅል ወደደ። አንደኛው የሰይጣንን ምክር ተከትሎ በአንድነት በአመጽ የሚኖረውን ዘር (ኤፌ 2፡ 1-3) ሲያሳይ; ሁለተኛው ደግሞ በጸጋው ከነዚህ አመጸኞች መካከል በእምነት እያዳነ ገንዘቡ የሚያደርጋቸው “ዘር” (ዕብ 11) ናቸው።

Note.....

a

i) በሁለት ዘር መካከል ልዩነት ይኖራል
ii) *የዚህ ልዩነት እግዚአብሔር "ጠላትነትን" ስላደረገ ነው*
iii) *በዚህ ጠላትነት/ ተቃርኖ ሁለቱም ዘሮች ይቆስላሉ! አንዱ ንጉስ ሆኖ ራስ ቀጥቃጭ ይሆናል (ሮሜ 16፡ 20 የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል;* Luke 10:17–19; Rev 12:11*)*

c) ይህ ተስፋ የቤተክርስቶያን አባቶች "የመጀመሪያይቱ-ወንጌል- Πρότο-εὐαγγελιον" ብለው ጠርተውታል። ይህ እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ከዚህ አመጽ ነጻ የሚያወጣ ዘር እንደሚሰጣቸው ተስፋ መግባቱ ነው

4) ይህን ተስፋ መጨበጣቸው አዳም ሚስቱን "የሕያዋን እናት" ብሎ መሰየሙ ነው
5) የዚህ ሁለት ዘር መከፈል እግዚአብሄር አገዛዙን በሁለት በኩል እንዲሆን አድረጎታል። አንደኛው በእምነት ፈቃዱን የሚፈልግ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነው ነገር ግን ይዚህ ከፉ ዘመን ነገስታት አድርጎ ሾማቸው።
   a) ቃየን ወንድሙን አቤልን ገደለ
   b) በአቤል ፈንታ እግዚአብሔር ለሔዋን "ሴትን" ሰጣች። የተስፋው ዘር ከሴት እንደሆን ሲያሳይ ዘፍ 5፡ 1 ያለው የአዳም ትውልድ በሴት ይቆጥረዋል

Note.....

a